ኢፕድ
# አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
82ኛ ዓመት ቁጥር 087 ኅዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# ለሁሉም የምትመች የጋራ ሀገር ለመፍጠር
## ምሑራን የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ
## ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሳሰቡ

**ውብሸት ሰንደቁ**



ፎቶ - ሳሙኤል ተስፋዬ

አዲስ አበባ፡- የጋራ የሆነች እና ለሁሉም የምትመች ሀገር ለመፍጠር ሁሉም ምሑራን የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አሳሳቡ፡፡ በትናንትናው ዕለት “ለኢትዮጵያ ልዕልና የምሁራን ሚና” በሚል መሪ ሀሳብ ሀገር አቀፍ የምሑራን የምክክር መድረክ በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

በምክክር መድረኩ ላይ የተገኙት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፤ መንግሥት ከምሑራን ጋር የሚሠራውም ሆነ ምሑራን ከመንግሥት ጋር የሚሠሩት ለጋራ የሀገር ጥቅም ነው፡፡ በመሆኑም የጋራ የሆነችና ለሁሉም የምትመች ሀገር መፍጠር ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

ምሑራን የሀገሪቱ ፖለቲካ በአደገኛ ነገሮች የታጀበ መሆኑንና ይህን የፖለቲካ ሥሪት ከግምት ውስጥ በማስገባት በወጉና በአግባብ የሚቀየርበትን መንገድ መከተል ይጠበቅባቸዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ይህን በማድረግ የጋራ የሆነች እና ሁሉም ሰው ሀብት የሚያፈራባትን ሀገር መፍጠር አለብን ሲሉ ገልጸዋል፡፡

“ኢትዮጵያ ሁላችን የምንከበርባት ሀገር መሆን ይገባታል፡፡ ሁላችንም ካልተከበርን ማናችንም ልንከበር አንችልም፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያውያን የሆንን ሁሉ ሠርተን ለፍተን የምናገኝበት ዕድል ማግኘት ይኖርብናል፡፡ ይህ ካልሆነ ሀገሪቷ ልትቀየር አትችልም፡፡ በዚህ ረገድ ምሑራን የበኩላቸውን ሚና ሊጫወቱ ይገባል” ሲሉ

ለሁሉም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የጳውሎስ ሆስፒታል ከ2ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የሚገነባቸው ማዕከላት 80 ከመቶ ደርሷል

- ማዕከላቱ ከአንድ ሺህ በላይ አልጋ የመያዝ አቅም አላቸው

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በሁለት ቢሊዮን 768 ሚሊዮን 21 ሺህ ብር ጠቅላላ በጀት ከሦስት ኮንትራክተሮች ጋር በመፈራረም የሚያስገነባቸውና ከአንድ ሺህ በላይ አልጋ የመያዝ አቅም ያላቸው የካንሰር እና የልብ ሕክምና ማዕከላት ሲቪል ሥራ ፊዚካል አፈፃፀም ግንባታ 80 በመቶ መድረሱን ተገለጸ፡፡ ሆስፒታሉ ተጨማሪ የድንገተኛ አደጋ ሕክምና ማዕከል ፕሮጀክት በአቤት ሆስፒታል ለመገንባትም 8600 ካሬ ቦታ ተረክቦ በዝግጅት ላይ መሆኑን አስታውቋል።

የጳውሎስ ሆስፒታል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## 100 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ የኤሌክትሪክ የብረት ማማዎች መሰረቃቸው ተገለጸ

**ኢያሱ መሰለ**



አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም ብቻ 100 ሚሊዮን ብር የሚገመቱ 756 ቶን የሚመዝኑ የኤሌክትሪክ የብረት ማማዎች ላይ ስርቆት መፈጸሙን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በሚያስተዳድራቸው የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር ተሸካሚ የብረት ምሰሶዎች ላይ ተደጋጋሚ ስርቆት እየተፈፀመ ነው፡፡

ተቋሙ 15 ሺ 467 ኪሎ ሜትር ርዝመት ወይም 20 ሺ 253 ኪሎ ሜትር የሰርኪዩት ርዝመት ያላቸው ከ132 እስከ 500 ኪሎ ቮልት የሚሸከሙ ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮች እንዳሉት የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፤ በአንድ ኪሎ ሜትር የሰርኪዩት ርዝማኔ በአማካይ ሶስት ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ የብረት ማማዎች እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

በ2014 ዓ.ም ብቻ 24 የሚደርሱ ከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊ የብረት ማማዎች ሙሉ ለሙሉ ተቆርጠው

100 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር
በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
– 0111 26 26 27 – 0922 11 53 24/26
– 0111 26 26 28 – 0922 72 74 48/49
– 0111 26 26 29 – 0922 72 38 70
– 0111 26 26 30 – 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ከወዳጅ ዘመዶቻችን ጋር ወደ ሁሉም የሀገር ውስጥ ኔትዎርክ እንደውል
ልዩ ጉርሻ
50 ብር | 120 ደቂቃ | 500 ሜጋ ባይት
100 ብር | 250 ደቂቃ | 1ጂቢ
200 ብር | 500 ደቂቃ | 4ጂቢ
ወደ ሁሉም የአገር ውስጥ ኔትወርክ መደወል የሚያስችለውን የድምጽ ጥቅል ለመግዛት ወደ *777# ይደውሉ
በተጠቀሙት ስከንድ ልክ የሚከፍሉባቸው ለ30 ቀናት የሚቆዩ ጥቅሎች ያልተገለገሉበትን ጥቅል የአገልግሎት ጊዜው ከማለቁ በፊት ሌላ ጥቅል በመግዛት ለቀጣይ ወር የሚያዘዋውሩበት
በአብሮነት ወደፊት
Safaricom
ሳፋሪኮም



የክልሉ ግብርና ምክትል ቢሮ ና ግብርና ዘርፍ ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ

## በክልሉ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ምርት ተሰብስቧል

- በመኸር እርሻ 203 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል
- ከበጋ ስንዴ 38 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

ገጽ 4




የፀረ ሙስና ኮሚቴው ርምጃ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ነዋሪዎች አሳሰቡ

ገጽ 3

# የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ፕሮጀክት 16 ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት ጀመሩ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በቅርቡ ወደ ኦፕሬሽን ከገቡ 16 የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ተርባይኖች 17 ነጥብ 7 ጊጋ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት መቻሉን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ።

የፕሮጀክቱ የጄኔሬሽን ኦፕሬሽን ሥራ አስፈጻሚ ጽሕፈት ቤት የፕላኒንግ ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ጥሩወርቅ ሽፈራው እንደገለጹት፤ የአይሻ 2 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት እያንዳንዳቸው 2 ነጥብ 5 ሜጋ ዋት የማመንጨት አቅም ያላቸው 48 የንፋስ ተርባይኖች የሚኖሩት ሲሆን ከዚህ ውስጥም የ32 የንፋስ ተርባይኖች የተከላ ሥራ ተጠናቋል። ከተተከሉት መካከልም 16ቱ ተርባይኖች ወደ ኦፕሬሽን ገብተው ኃይል ማምረት ጀምረዋል። በአሁኑ ጊዜም 17 ነጥብ 7 ጊጋ ዋት ሰዓት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ተችሏል፡፡

ይህም ከዕቅዱ በላይ መሆኑን የገለጹት ሥራ አስኪያጇ፤ ተርባይኖቹ ከዕቅድ በላይ ለማመንጨታቸው በአካባቢው ያለው የንፋስ ኃይል ፍጥነት ከፍተኛ መሆኑንም በምክንያትነት አንስተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ወደ ኦፕሬሽን በገቡ የንፋስ ተርባይኖች የመነጨው ኃይል፤ ከሌሎች መሰል ጣቢያዎች የተሻለ ኃይል ማምረት እንደሚቻል ያሳየ እንደሆነም ጠቁመዋል።

ከፕሮጀክቱ በአሁኑ ወቅት የተገኘው ምርት እስካሁን ወደ ኦፕሬሽን ከገቡ ሌሎች የንፋስ ማመንጫ ጣቢያዎች ጋር ሲነጻጸር በመጀመሪያ ጊዜ ይህን ያህል ኢነርጂ ያመነጨ ጣቢያ እንዳልነበረም ወይዘሮ ጥሩወርቅ አስታውሰዋል።

ይህም ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ የታቀደለትን የማመንጨት አቅም እንደሚያሳካ እና ወደ ፊት ወደ ኦፕሬሽን የሚገቡ ቀሪ የንፋስ ተርባይኖች አስተማማኝ የሆነ ኃይል እንደሚያመነጩ ተስፋ የሰጠ እንደሆነ መናገራቸውን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ከንፋስ የሚገኘውን የኃይል ምንጭ ለማሳደግ በአይሻ 2 አካባቢ ያለው አማካኝ የንፋስ ፍጥነት ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ወይዘሮ ጥሩወርቅ ገልጸዋል።

# ኮንትሮባንድን ለመከላከል በተሠሩ ቅንጅታዊ ሥራዎች ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ ማዳን ተችሏል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ኮንትሮባንድን እና ሕገወጥ ንግድን ለመከላከል በተሠሩ ቅንጅታዊ ሥራዎች ሀገር ልታጣ የነበረውን 15 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ማዳን መቻሉን የጉምሩክ ኮሚሽን አስታወቀ።

ኮሚሽኑ ባለፉት ጊዜያት በተጠናከረ መልኩ ከፌደራል ፖሊስ፣ ከንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ ከማዕድን ሚኒስቴር፣ ከብሔራዊ መረጃና ደህንነት እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሠራ እንደሚገኝ የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ ገልፀዋል።

የወጭ ይሁን የገቢ ኮንትሮባንድን ለመከላከል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ቢሆንም አሁንም በዚህ ጉዳይ ላይ የሚታዩ ተግዳሮቶች እየበዙ መምጣታቸውን ተናግረዋል።

አሁን ላይ የጫት ኤክስፖርት በከፍተኛ ደረጃ ጉዳት እያደረሰ ያለ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ከዚህ ባለፈ በእንስሳት የሕገ ወጥ ንግድ፣ በግብርና ምርቶች እንዲሁም በማዕድን ዘርፍ ሀገር ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎች መኖራቸውን ገልፀዋል።

በመንግሥት መዋቅር ውስጥ የሚገኙ አካላት ከእነዚህ የኮንትሮባንድ አንቀሳቃሾች ጋር ተሳታፊ መሆናቸው ቁጥጥሩን ከባድ እንደሚያደርገውም ተናግረዋል።

አሁን ላይ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ሽፋን አድርገው ባለማወቅም ይሁን ሆን ብለው ትስስር በመፍጠር የሀገርን ሀብት በሕገ ወጥ መንገድ የሚበዘብዙ አካላት መኖራቸውን ኮሚሽነሩ አብራርተዋል።

ከንግድ ማጭበርበር ጋር በተያያዘ ብዙ ፈታኝ ጉዳዮች መኖራቸውን ያነሱት ኮሚሽነሩ፤ በተለይም ሕጋዊ ገቢ እቃዎች በተመለከተ በተለያዩ መንገዶች ለከፍተኛ የማጭበርበር ድርጊቶች እንደሚጋለጡ ተናግረዋል።



**አቶ ደበሌ ቃበታ**

የጉምሩክ ኮሚሽን በእነዚህ እቃዎች ላይ የሚሠራውን የሰፋ የንግድ ማጭበርበር ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን እና አሠራሮችን ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝ ኮሚሽነሩ ተናግረዋል።

እንደ ሀገር የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴዎችን እና ሕገ ወጥ የንግድ ሥራዎችን በሚገባ ለመቆጣጠር እና ለመከላከል በቅድሚያ ችግሩን የማወቅ አቅም መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በዚህ ላይ በመመርኮዝም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ ሰንሰለት በመፍጠር መሥራት ይገባል ብለዋል።

ይህ ውጤት በተለይም በኢንተለጀንስ፣ በድንገተኛ ፍተሻ፣ በመደበኛ የፍተሻ ሥራዎች እና የቀረጥ ነፃ መብትን አላግባብ በተጠቀሙ አካላት ላይ በተወሰዱ እርምጃዎች የተገኘ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህ የተቀናጀ የሕግ ተገዢነትን የማረጋገጥ ተግባር ተጠናክሮ እንደሚቀጠል መግለጻቸውን ኢቢሲ ዘግቧል።

# የሰላምና የልማት ሥራዎችን ለማሳካት የወረዳ መጅሊስ አመራሮች በትጋት እንዲሠሩ ጥሪ ቀረበ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በዘላቂነት ለሚከናወኑና ሀገራዊ የሰላምና ልማት ሥራዎች ለማሳካት የወረዳ መጅሊስ አመራሮች ዝግጁ እንዲሆኑ የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ጥሪ አቀረበ፡፡

የጠቅላይ ምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን አማን ለወረዳ የመጅሊስ አመራሮች ባቀረቡት ጥሪ እንደተናገሩት፣ በኢትዮጵያ በዘላቂነት ለሚከናወኑ ሀገራዊ ጠቀሜታ ላላቸው የሰላምና የልማት ሥራዎች በሁሉም ወረዳዎች የሚገኙ የመጅሊስ አመራሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ እንዲዘጋጁ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ፕሬዚዳንት ሼህ ሱልጣን፣ ለአመራሮቹ የሚደረግላቸው ቅድመ ዝግጅት የሚፈጠረውን ድካምና መሰላቸት እንደሚያስቀርና ለሀገር ብሎም ለእምነቱ እንዲበጁ በሚከናወኑ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የሀገር ሰላምና ልማት ሥራዎች ላይ በዘላቂነት ለመሥራት እንደሚያግዝ ጠቁመው፤ ሥራዎቹን በተቀናጀ መልኩ ከግብ ለማድረስ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

የሚደረገው ዝግጅትም ቀጣይ በዘላቂነት ለሚከናወኑና ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው የሰላምና ልማት ሥራዎች የሀገሪቱንና የሕዝበ ሙስሊሙን የመሠረተ ልማትና ሌሎች ግብዓቶች በቀላሉ ለማሟላት የሚያስችል መሆኑን ፕሬዚዳንቱ አመላክተዋል፡፡

ዝግጅቱ በዘላቂ የሰላምና ልማት ሥራዎች በምናደርገው ሥራ ለምክር ቤቱ የገቢ ማስገኛ የሚሆኑ ሥራዎችን ለማከናወንና በታሰበላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ ያስችላል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ሼህ ሁሴን በሽር በበኩላቸው፣የመጅሊሱ አመራሮች በሚያደርጉት ቅድመ ዝግጅት ወደ ሥራ ሲገባ አዳማ በሚገኘውና ተቋርጦ በመጅሊሱ እንደ አዲስ መዋቀር የተጀመረው የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክትን ሥራ አጠናክሮ አስቀጥሏል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ አንዋር መስጅድና በአፍሪካ ኅብረት አጠገብ የሚገነባው የነጃሺ ኢስላማዊ ማዕከል የሜጋ



**ሼህ ሱልጣን አማን**



**ሼህ ሁሴን በሽር**

ፕሮጀክቶች ግንባታዎች እንዳሉና ሥራቸውን ቀልጣፋ ማድረግ እንዲሚሻ ገልፀዋል።

በአፍሪካ ኅብረት አጠገብ የሚገነባው የነጃሺ ኢስላማዊ ማዕከል የሜጋ ፕሮጀክቶች ግንባታን አስመልክቶ የግንባታ ዲዛይኑ መጠናቀቁን ዋና ፀሐፊው አብስረዋል፡፡

ቀድመው በመጅሊሱ የቀረቡ የመካነ-መቃብር ቦታዎች ጥያቄና በተለያዩ ቦታዎች የሚገነቡ የማስፋፊያ ሥራዎችና ሌሎችም ጠንካራ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ፀሐፊው፣ ለመዲናዋ ነዋሪዎችና ለሕዝበ ሙስሊሙ የሚያገለግሉ 47 የመስጂድና የመካነ-መቃብር ቦታ የመጨረሻ የውሳኔ ጥያቄ ለከንቲባ ጽሕፈት ቤት ማቅረባቸውንም አመልክተዋል፡፡

ዜና

# የፀረ ሙስና ኮሚቴው እርምጃ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ነዋሪዎች አሳሰቡ


አቶ ሳሙኤል ወልደ ማርያም


ወይዘሮ ታደለች ታንቱ


አቶ ፀጋ ካሳዬ


ወጣት ኤሊያስ ሚካኤል

ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሙስና ለመልካም አስተዳደር እንቅፋት በመሆኑ እንደባህል ልንጸየፈውና ሙስናን በሚፈጽሙ አካላት ላይ መንግሥት የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ እንዲቀጥል የአዲስ አበባ ነዋሪዎች አሳሰቡ።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣት ኤሊያስ ሚካኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ ሙስና ለመልካም አስተዳደር፣ ለእኩልነትና ለሕዝባዊ አንድነት እንቅፋት ከመሆን አልፎ የሀገር እድገት ማነቆ በመሆኑ ልንጸየፈው የሚገባ ተግባር ነው።

በቅርቡ የተቋቋመው ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ በሙስና የተጠረጠሩ አካላት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን አስታውቋል ያለው ወጣት ኤልያስ፤ ኮሚቴው የሚወስደውን እርምጃና ቁጥጥር አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብሏል። ሙስና ከኑሮ ውድነትና ሥራ አጥነት ቀጥሎ የሀገር ደህንነት ሥጋት መሆኑንም ገልጸዋል።

ስለሙስና በቤተ-እምነትና በትምህርት ተቋማት ግንዛቤ ካልተሰጠ የሚጠበቀውን ለውጥ ለማምጣት አዳጋች ነው። ሙስና አስተሳሰብን የሚለውጡ እውቀቶችን የሚፈልግ በመሆኑ በቤተ-እምነትና በትምህርት ተቋማት ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

በትምህርት ተቋማትና በእምነት ተቋማት ሙስና የሚያስከትለውን ጉዳት ለኅብረተሰቡ በማስተማር ቀጣዩን ትውልድ ከሙስና የጸዳ ማድረግ ይቻላል ያለው ወጣት ኤሊያስ፤ ይህንን ለማድረግ ረጅም ጊዜን የሚፈልግ በመሆኑ ለልጆች የዕለት ተዕለት ክትትል ማድረግ አስፈላጊ ነው ብሏል።

እያንዳንዱ ወጣት በተሰማራበት ዘርፍ ሀገር የሰጠችውን ኃላፊነቱን የሚወጣ ከሆነ ሀገር ከሙስና ነፃ የማትሆንበት ሁኔታ የለም ያሉት ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወይዘሮ ታደለች ታንቱ ናቸው።

ሙስና ባይኖር ሀገሪቱ የምትደርስበትን ደረጃ ማወቅ ይቻላል። የሚባክነው የሀገር ሀብት ነው። ይህም እንደ ሀገር ከፍተኛ ውድቀት ያስከትላል። ኢትዮጵያም ላለፉት ዓመታት በርካታ ችግሮች እንድታሳልፍና ድህነት ላይ እንድትወድቅ ያደረጋት ሙስና ነው ብለዋል።

ሙስናን ማጥፋት የመንግሥት ብቻ ኃላፊነት አይደለም። መንግሥት የተሰጠው ኃላፊነት እንዳለ ሁሉ ኅብረተሰቡም መወጣት የሚገባው ኃላፊነት አለ። ከዚህም ውስጥ አንደኛው ሙስና የሚፈጽሙ ሰዎችን ማጋለጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ ስለሙስና ከመንግሥት የሚሰጡ ስልጠናዎችን ተግባራዊ ማድረግ ነው ብለዋል። መንግሥት ሙስናን ለመከላከል የሚያደርገው ጥረት የሚደገፍ ነው ሲሉም ወይዘሮ ታደለች ተናግረዋል።

ሌላው የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ ሳሙኤል ወልደ ማርያም እንደተናገሩት፤ ችግሩ ከመንግሥት አልፎ እያንዳንዱ ቤት እየገባ በመሆኑ ኅብረተሰቡ በአንድነት ድምፁን በማሰማትና ከመንግሥት የሚሰጡ መመሪያዎችን በመተግበር ሙስናን ለማጥፋት መጣር አለበት።

አብዛኛውም ጊዜ መንግሥት እርምጃ አይወስድም ይባላል። ነገር ግን ሙስና መንግሥትና ኅብረተሰቡን እንዲሁም ሀገርን የሚጎዳ ነው። ይህንን ለማጥፋት ደግሞ የሕዝቡ ቆራጥነት ወሳኝ ነው ብለው፤ ሚዲያው ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ በማስጨበጥና ሙሰኞችን በማጋለጥ መሳተፍ አለበት ብለዋል።

ከዚህም ባለፈ ኅብረተሰቡ መንግሥትን የሚያበረታታና ለተግባራዊነቱ የሚጠበቅበትን መስዋዕትነት የሚያዳርግ ከሆነ እንደ ሀገር ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ አቶ ፀጋ ካሳዬ በበኩላቸው፤ ሙስና በሀገር ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። በአንድ ሀገር ላይ በሙስና የሚሠራ ሥራ ተበራከተ ማለት የሀገር ኢኮኖሚ አሽቆለቆለ ማለት ነው። ስለዚህ ወጣቱ ከሙስና ጋር ተያይዘው የሚፈጠሩ አላስፈላጊ ተጽዕኖዎችን ማጋለጥ አለበት።

ስለዚህ በመንግሥት በኩል የተጀመረው ሥራ የሚደገፍ ነው። ኅብረተሰቡም በሙስና እየተበዘበዝኩ ያለሁት እኔ ነኝ በሚል ስሜት መነሳትና መብቱን በሕጋዊ መንገድ ለማግኘት መጣር ይኖርበታል ብለዋል።

ሁለተኛ ደግሞ ሙሰኞችን በሚያገኙበት ሰዓት ለሚመለከተው አካል ማጋለጥ አለበት በማለት መንግሥት እየሠራ ያለውን ሥራ ማጠናከር እንደሚገባው አሳስበዋል።

# "ሀገራት በኢኮኖሚ ለማደግ የበይነ መረብን አዎንታዊ ጥቅም ሊገነዘቡ ይገባል"

**- ቬንት ሰርፍ**

**ሞገስ ተስፋ**


ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- ሀገራት በኢኮኖሚ ለማደግ የበይነ መረብን አዎንታዊ ጥቅም ሊገነዘቡ እንደሚገባቸው የኢንተርኔት አባት በመባል የሚታወቁት ቬንት ሰርፍ ገለጹ። አፍሪካውያን በይነመረብን ለልማት በመጠቀም ከሐሰተኛ መረጃዎች ራሳቸውን ሊጠብቁ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

ቬንት ሰርፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በይነ መረብ ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አወንታዊ ጠቀሜታ እጅጉን እያደገ መጥቷል። ያም ሆኖ ግን አሉታዊ ጎኖችን መከላከል ችላ ሊባል አይገባውም።

ዓለም በቴክኖሎጂ በተሳሰረበት ዘመን የሐሰተኛ መረጃን በበይነመረብ በመልቀቅ ችግር ሲፈጠር ይስተዋላል። ይህም ነገሮችን በጥልቀት ካለማሰብ የሚመነጭ ነው። ማኅበረሰቡ የሐሰተኛ መረጃዎችን ከመውሰድ ይልቅ ለምን እንደሚለቀቁ ማገናዘብ አለበት። የሚወጡ መረጃዎችን ከየት፣ እንዴት፣ ከማንና ለምን እንደተለቀቁ ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ በመጠቀም ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።

ሰርፍ፤ ሐሰተኛ መረጃዎች፣ በጋዜጦች፣ በዩቲብ፣ በቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና መሰል የበይነመረብ አውታሮች ሊሰራጭ ይችላል። ስለዚህ በጥልቀት የማሰብና የማሰላሰል ልምድ በማዳበር ሐሰተኛ መረጃዎችን መለየት እንዲችል የግንዛቤ ሥራ ሊሠራ ይገባል። ሐሰተኛ መረጃዎችን ለማሰራጨት ለምን ይፈልጋሉ የሚለው ሊጠናና እልባት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው። ሐሰተኛ መረጃ ሕዝብ የተዛባ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያደርግ ነው። ስለዚህ የሐሰተኛ መረጃ ውጤቱን ማሰብ ጠቃሚ ነው ብለዋል።

በስሜት የሚለቀቁ የሐሰተኛ መረጃዎች በተለይም የአፍሪካ ሀገራትን ይጎዳሉ ያሉት ሰርፍ፤ ሀሳቡን ከመውሰድ በፊት ስለመረጃው ግራና ቀኝ ማየት አስፈላጊ ነው ብለዋል። በተለይም ትኩስ ኃይል የሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል መረጃዎችን እንደወረዱ መውሰድ ሳይሆን እንዴት ልውሰድ በማለት ማሰብ አለበት፤ ሳይንሱ የሚነግረንም ነገሮችን በማሰላሰል እንድንመለከት ነው ብለዋል።

በኢኮኖሚ ለማደግ ካስፈለገ አቅም ያለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት ሊኖር ግድ ይላል። ያደጉ ሀገራት ለደረሱበት ደረጃ ትልቁ ሚስጥር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀማቸው ነው። አፍሪካም ይህን ለማድረግ ትልቅ አቅም አላት። በተለይም በሌሎች ዘርፎች አልሚዎችን እንደሚስቡ ሁሉ በቴክኖሎጂ ዘርፍም መሳብ ቢችሉ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ሲሉም ተናግረዋል።

የኢንተርኔት አባቱ እንደገለጹት፤ ሀገራት በኢኮኖሚ ለማደግ የበይነመረብን አዎንታዊ ጥቅም ሊገነዘቡ ይገባል። በተለይ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በአግባቡ መሠረተ ልማት አሟልተው መጠቀም አለባቸው። 17ኛው የዓለም የበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ ትልቅ ግብዓት የተገኘበት ነው። ኢንተርኔት ዘርፈ ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ነው። የአገር በቀል ኢኮኖሚን ለማሻሻል ኢንተርኔት አስፈላጊ ነው። ኢትዮጵያ በዘርፉ ትልቅ ሥራ እየሠራች ሲሆን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንቨስት ማድረግ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ መሆን አለበት።

ሰርፍ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የበይነመረብ ጉባኤን በሚገባ አስተናግዳለች። ከዚህም ባሻገር የበይነመረብን ተደራሽነት ለማሳደግ እያደረገችው ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው።‹‹ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ በለጠ ሞላ (ዶክተር) ጋር በሰፊው ተወያይተናል። አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ በቂ የመሠረተ ልማት ተደራሽነት ሊኖር ይገባል። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ለምታደርገው ጥረት የቻልኩትን ድጋፍ አደርጋለሁ›› ሲሉ ሰርፍ ገልጸዋል።


ፎቶ - እዮብ ተፈራ

# ሠራዊቱ በከተሞች ውጊያ እንዳይካሄድ ያደረገውን ጥንቃቄ ዓለምአቀፉ ቀይ መስቀል ማኅበር አደነቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከደቡብ አፍሪካው የሰላም ስምምነት በፊት በሰሜኑ ጦርነት ወቅት በከተሞች ውጊያ እንዳይካሄድ በማድረጉ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ምስክርነቱን ሰጥቷል ሲሉ የመከላከያ ሠራዊት የውጭ ግንኙነትና ወታደራዊ ትብብር ዳይሬክተር ጄኔራል ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ ገለጹ።

ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገመቹ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በኢንዶኔዥያ ባሌ ከተማ በተደረገ የመከላከያና የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል አመራሮች መድረክ ላይ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በከተሞች አካባቢ ያደረገው ጥንቃቄ አድናቆት ተችሮታል።

በመድረኩ የተገኙት የዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ጊልስ ካርቦኒየር የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በርካታ ሕዝብ በሚሰበሰብባቸው ከተሞች ውጊያ እንዳይደረግ ያደረገው ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራ የሚደነቅ ነው ማለታቸውን ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ተናግረዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንቱ በተለይም በሽሬ ከተማ የሚገኙ የቀይ መስቀል ሠራተኞችን እማኝ አድርገው ባቀረቡት ምስክርነት ከተማዋና ሕዝቦቿ እንዳይጎዱ መከላከያ ሠራዊት ያደረገው ጥረት የዓለም አቀፍ ሕግ ከሚጠይቀው በላይ ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ መሆኑን መመስከራቸውን ጠቁመዋል።

በጦርነት ወቅት የሰብዓዊ ጉዳትን መቀነስን በተመለከተ ዓላማ አድርጎ በኢንዶኔዥያ ባሌ ከተማ ስለተደረገው የዓለም አቀፍ መድረክ ከ85 አገራት የተውጣጡ የመከላከያ አመራሮች የተሳተፉበት ነው፤ በመድረኩ የኢትዮጵያ ስም በበጎ ሁኔታ ለሌሎችም ተሞክሮ በሚሆን መንገድ መቅረቡን ሜጀር ጀኔራል ተሾመ ተናግረዋል።

በከተሞች አካባቢ የሚደርሰውን ጉዳት መቀነስ እንደሚገባ የዓለም አቀፍ ሕግጋት ያዛሉ ያሉት ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ፤ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ግን ጉዳት መቀነስ ሳይሆን ጥፋትን ማስቀረት በሚል በሰሜኑ ጦርነት ከተሞች አካባቢ ውጊያዎችን ማስቀረቱን ገልጸዋል።

ይህን የሠራዊቱን ጥረት የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብም መመስከር ጀምሯል። ውጤቱ የተገኘውም በመከላከያ አመራሮች ጠንካራ የዕቅድ፣ ክትትልና አፈጻጸም ሂደት ነው ብለዋል።

ለውጤታማነቱም ከሠራዊቱ አመራሮች ባለፈ ግዳጃቸውን በጥንቃቄ በመፈጸም ብቃታቸውን ያሳዩ የመከላከያ አባላትም ምስጋና ይገባቸዋል ሲሉ ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ተናግረዋል።

የመከላከያ በከተሞች አካባቢ ጦርነቶችን ለማስቀረት የሄደበት መንገድ የሠራዊቱን ልምድና ሙያዊ ሥነምግባር ያሳደገ መሆኑን ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገልጸዋል።

እንደ ሜጀር ጄኔራል ተሾመ ገለጻ፤ የአንድ ሠራዊት ብቃትና ሙያዊ ሥነምግባር ከሚለካባቸው መንገዶች አንዱ ዓለም አቀፍ ሕግጋትን እያከበረ የተሰጠውን ግዳጅ መፈጸም ነው።

በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አስፈላጊውን ሙያዊ ብቃት ከጊዜ ወደጊዜ ማሳደጉን ያሳያል። ሠራዊቱም ቀድሞም ቢሆን በከተሞች አካባቢ ጉዳትን ከማስቀረት ጋር በተያያዘ በርካታ ሥራዎችን አከናውኗል፤ ይህ ሙያዊ ግዴታም ይቀጥላል ሲሉ ተናግረዋል።

የመከላከያና የቀይመስቀል አመራሮች የተሳተፉበት የኢንዶኔዥያው መድረክ እ.ኤ.አ ከኅዳር 20-26 ቀን 2022 ተካሂዷል።

ዜና

# በክልሉ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ምርት ተሰብስቧል

- በመኸር እርሻ 203 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል
- ከበጋ ስንዴ 38 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በመኸር እርሻ በዘር ከተሸፈነ ማሳ እስከ አለፈው ሐሙስ ድረስ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ምርት መሰብሰቡን የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በዘንድሮ የመኸር እርሻ 203 ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅና ከበጋ ስንዴ ደግሞ 38 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ጠቁሟል።

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በሪሶ ፈይሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ ክልሉ መረጃው እስከተጠናቀረበት እስከአለፈው ሐሙስ ድረስ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ ምርት መሰብሰቡንና ከተሰበሰበው ሰብል ሠላሳ ሚሊዮን ኩንታል የተጣራ ምርት መገኘቱን ገልጸዋል።

ክልሉ በአጠቃላይ በመኸር በዘር ከተሸፈነው ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ሁለት መቶ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ አቅዶ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል። በአሁኑ ሰዓት ምርት በደረሰባቸው ቦታዎች ሁሉ ኅብረተሰቡ ምርት የማሰባሰብ ሥራ እያካሄደ ነው። ኅብረተሰቡ ምርቱን ሳይባክን የአካባቢውን ጉልበትና በኮምባይነር ለመሰብሰብ የሚያስችል ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ሠርቷል። ከአምስት መቶ በላይ ኮምባይነሮች ምርት ማሰባሰብ ላይ ተሰማርተዋል፣ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር በአጠቃላይ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ መጠቀም መቻሉን ገልጸው በተጓዳኝ የመስኖ እርሻ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑንም አያይዘው ገልጸዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ መስኖ ሥራው በመደበኛ መስኖና በበጋ ስንዴ ትኩረት ተደርጎ ዝግጅት እየተደረገ ነው። በመደበኛው መስኖ በተለያዩ የእህል ዓይነቶች በዘር ለመሸፈን በእቅድ ከተያዘው 514 ሺህ 765 ሄክታር ውስጥ 154 ሺህ 565 ሄክታር ታርሷል፣ 112 ሺህ 670 ሄክታር በዘር ተሸፍኗል ።

ከበጋ ስንዴ 38 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት አንድ ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈን ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል። እስከ አሁን ድረስ በተሠራው ሥራ 600 ሺህ ሄክታር መሬት ተዘጋጅቷል ፣ 300ሺህ ሄክታር በዘር ተሸፍኗል ። ለበጋ ስንዴ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር ምርጥ ዘርና አስፈላጊ ግብዓቶች ለአርሶ አደሩ እየቀረበ ነው። ተጨማሪ ግብዓቶች ግዥ እየተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል።

በተያያዘ ዜና አረንጓዴ አሻራ ልማት የአፈር መሸርሸር በመከላከል የአፈር ለምነት በመጠበቅ ምርትና ምርታማነት ለመጨመር አስተዋፅዖ እያበረከተ መሆኑን ገልጸዋል ። በአሁኑ ሰዓት ተፋሰስ አካላት ውሃ የመያዝ አቅማቸው በመጨመሩ የአካባቢውን ደን ወደ ነበረበት እንዲመለስ በማድረግ የአካባቢውን ሥነምሕዳር በማስተካከል ተስፋ ሰጪ እምርታዎች በምርት አሰባሰቡ እየታየ ነው ብለዋል ።

በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያዎችና አመራሮች በሚሰጡት አቅጣጫ መሠረት ኅብረተሰቡ የአካባቢውን ጉልበትና ኮምባይነር በመጠቀም ምርት ሳይባክን እንዲሰበስቡ ጥሪ አቅርበዋል።



# ባለፉት አራት ወራት ቡናን ወደ ውጭ በመላክ 526 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተገኝቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አራት ወራት ቡናን ወደ ውጭ በመላክ 526 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ኮሎምቢያና ስፔንን ጨምሮ ከተለያዩ ቡና አምራች ሀገራት ባለሙያዎች ጋር በአዲስ አበባ እየመከረ ይገኛል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አዱኛ ደበላ በመድረኩ የበጀት ዓመቱን አራት ወራት የኢትዮጵያን የቡና ምርት ግብይት በተመለከተ ገለፃ አድርገዋል።

ባለስልጣኑ በበጀት ዓመቱ ቡናን ወደ ውጭ በመላክ 2 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ ለማግኘት አቅዶ እየሠራ መሆኑን አስታውሰው ባለፉት አራት ወራት ወደ ውጭ ከተላከ የቡና ምርት 526 ሚሊዮን ዶላር ማግኘት መቻሉን ገልጸዋል።

በዘንድሮው በጀት ዓመት 810 ሺህ ቶን የቡና ምርትን ወደ ውጭ በመላክ 2 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ገቢ ለማግኘት መታቀዱን ጠቁመው የእስካሁኑ እንቅስቃሴ አበረታች ነው ብለዋል።

በበጀት ዓመቱ የተቀመጠውን ዕቅድ ለማሳካት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ ኢዜአ ዘገባ የዘንድሮው የአራት ወራት አፈጻጸም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ126 ሚሊዮን ዶላር ብልጫ እንዳለውም አስታውቀዋል።

## ለሁሉም የምትመች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠቁመዋል፡፡

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና በበኩላቸው፤ ምሑራን የሀገሪቱ ሉዓላዊነት፣ ለሰላምና ብሔራዊ ጥቅም አስቀድመው ሊሠሩ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ምሑራን ምንም ያህል አካሄዳቸው ቢለያይም ድምሩ የአንድ ሀገርን ብልፅግና ማረጋገጥ መሆኑን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህንን ማሳካት የሚቻለው ከምንም በላይ የሀገር ጥቅምን በማስቀደምና በመሥራት መሆኑን ተናግረዋል።

ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም የአንድነትና የሉዓላዊነት መሠረት መሆኑን መገንዘብ ይገባል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ምሑራን በሚሠሩት ሥራ ይህን መተግበር እንደሚገባቸው አመላክተዋል። በዚህም ተማሪዎችን በሀገር ፍቅር በመቅረፅና በዓለም አቀፍ መድረክ ተፅዕኖ መፍጠር ከምሑራን ይጠበቃል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጀ እንግዳ በሰጡት የማጠቃለያ ሃሳብ ለኢትዮጵያ ልዕልና የምሑራን ሚና መድረክ መዘጋጀቱ ተገቢነት እንዳለው ገልጸዋል፡፡

በቀረቡት የዳሰሳ ጥናቶች እና የውይይት መነሻ ሃሳቦች የምሑራን ሚና በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እንዲሁም በኢትዮጵያ ሰላምና መረጋጋት ላይ አስተዋፅዖ ዝቅተኛ እንደሆነ መጠቆሙ ተገቢነት ያለውና ለሁላችንም ገዢ ሊሆን የሚችል አስተያየት ነው ብለዋል፡፡

በተቋማት የምሑራን መወያያ ክበባትንና አጀንዳዎችን በመቅረፅ እንዲሁም መድረኮችን በማስፋፋት ምሑራን ለሀገር ዕድገት፣ ሉዓላዊነት እና ሰላም መረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማድረግ እንደሚሠራም ጠቁመዋል፡፡

በመድረኩ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ ሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት እንዲሁም ከልዩ ልዩ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ምሑራን የተገኙ ሲሆን መድረኩን ያዘጋጁት የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርስቲ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በመቀናጀት መሆኑ ታውቋል።

## የጳውሎስ ሆስፒታል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሆስፒታሉ የምሕንድስናና ግንባታ ዳይሬክተር የሆስፒታሉ ኢንጂነር አማኑኤል ሕይወት በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሆስፒታሉ ከ1 ሺህ በላይ አልጋ ያለው ብሔራዊ የካንሰር፤ የልብ እና ከሆድ ዕቃ ጋር ተያያዥ (የአንጀት፣ ጨጓራ፣ ጉበት) ሕክምና ማዕከላትን እያስገነባ ይገኛል፡፡

በ6800 ካሬ በላይ ያረፈው ብሔራዊ የካንሰር ሕክምና ማዕከል በየክልሉ ከሚገኙት የካንሰር ማዕከላት የገዘፈና ለጨረር ሕክምና የሚሆን 5 ባንከር ያለው ነው። በጨረር ሕክምና ለካንሰር ሕክምና አገልግሎት የሚውለው ባንከር ጣሪያው ብቻ የቀረው ሲሆን፤ የካንሰር ሕክምና ማዕከሉ ከ337 በላይ አልጋ ያለው ነው፡፡ ከኖርማል ራድዮሎጂ ዩኒት፣ ኤም አርአይ፣ ሲቲ ስካን በተጨማሪም ኒውክላር ሜዲሰን ያለው ነው ሲሉም ኢንጂነር አማኑኤል አብራርተዋል።

በመደበኛ ኢሜጂንግ የማይታዩ የካንሰር ዓይነቶችን በግልጽ ለማየት የሚያስችሉ በኮንክሪት የተሠሩና የተለየ ቦታ የሚቀመጡ ቴክኖሎጂዎች መካተታቸውንም ጠቁመዋል።

እንደ ኢንጂነር አማኑኤል ማብራሪያ በ1900 ካሬ ላይ ያረፈው ባለ ስምንት ወለል ሕንጻ የልብ ሕክምና ማዕከል ፕሮጀክትም እራሱን ችሎ ከ316 በላይ አልጋ፤ 15 አይሲዩ እና 15 ሲሲዩ አልጋዎች እንዲሁም አራት የቀዶ ጥገና፤ ሁለት ካትላብ እና 10 የማገገሚያ ክፍሎች ያሉት ቤዝመንትና ባለ ስምንት ወለል ያለው ሕንጻ ይገኝበታል።

በ1400 ካሬ ላይ ያረፈውና የአንጀት፣ ጨጓራ፣ ጉበትና ተያያዥ ሕክምና ማዕከል የሆነው፣ 184 አልጋዎች፣ ስድስት የጨጓራ ምርመራ (ኢንዶስኮፒ) ሩም ያለው ሲሆን ቤዝመንትና ስምንት ወለል ያለው ሕንጻ ነው። ሙሉ ከአንገት በላይ ሕክምና ከቦታ ችግር ጋር ተያይዞ ራሱን ችሎ ሊገነባ ባለመቻሉም 115 አልጋዎች ያሉት የራሱ ኦፕሬሽን ክፍል ያለው፣ በአንዱ ብሎክ የተካተተ መሆኑንም አመላክተዋል።

ፕሮጀክቱ ከሦስት ኮንትራክተሮች ጋር በተደረገ ስምምነት እየተገነባ የሚገኝ ሲሆን ታኅሳስ 2008 የተፈራረመው ዋና ሲቪል ኮንትራክተር የሆነው አስመላሽና ልጆቹ ከአንድ ቢሊዮን 689 ሚሊዮን በላይ ብር በሆነ በጀት ተፈራርመው የተጀመረ መሆኑን አስታውሰዋል።

ካሳለፍነው ሰኔ ወር ጀምሮ ከሆስፒታሉ ጋር የአንድ ዓመት ኮንትራት የተፈራረመው ባማኮን ኢንጂነሪንግ ከካንሰር ሕክምና ጋር የተያያዙ ዘመናዊ የኔትወርክ ዝርጋታ፣ በኔትወርክ የተደገፈ የሕንፃ ማኔጅመንት ሲስተም፣ ነርስ ኮል ሲስተም፣ አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን እና የማጠናቀቂያ ሥራዎችን ጨምሮ በ789 ሚሊዮን ብር እየሠራ የሚገኝ ነው። ከሐምሌ 2013 እስከ ሚያዝያ 2015 ለማጠናቀቅ 289 ሚሊዮን 773 ሺህ ብር የተፈራረመው ኪቢሽ ኮንስትራክሽን የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራውን እየሠራ የሚገኝ መሆኑንም አመላክተዋል።

ከዋጋ ንረት አንጻር የሲሚንቶና የብረት ችግር በመጠኑ ተግዳሮት እንደሆኑበትም ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል። ጨረር ለመከላከል የሚሠራው ባንከር ግንባታ ጣራ ሥራ ይቀራል ያሉት ዳይሬክተሩ ተቆራርጦ የማይሞላና 5ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ የሚፈጅ ኮንክሪት በአንድ ጊዜ የሚሞላ መሆኑንም አስረድተዋል። በዋናነት ግን የመጨረሻ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመቱ ዕቃዎች ሙሉ ከውጭ የሚገቡ በመሆኑ በጤና ጥበቃ በኩል ከሦስት ወር በፊት 15 ሚሊዮን ዶላር ለብሔራዊ ባንክ የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎ በመጠባበቅ ላይ መሆኑንም አስታውሰዋል።

የድንገተኛ አደጋ ሕክምና ማዕከል በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አካል በሆነው አቤት ሆስፒታል በአነስተኛ ሕንጻ በኪራይ ትልቅ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ መሆኑን አስታውሰዋል። 8600 ካሬ ሜትር መሬት ከጉለሌ ክፍለ ከተማ በመውሰድ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና ማዕከል ሜጋ ፕሮጀክት ግንባታ ዲዛይን ተጠናቆ ከሦስት ወር በኋላ ግንባታው የሚጀመር መሆኑንም ጠቁመዋል።

## 100 ሚሊዮን ብር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የወደቁ ሲሆን የብረትና የኮንዳክተር ዘረፋ እንደተፈጸመባቸው እና በቁጥር 30 ሺ 257 የሚሆኑ የተለያዩ የታወር ብረቶች ደግሞ በቆሟቸው ካሉ ማማዎች ተፈታተው መወሰዳቸውን ገልጸዋል፡፡

ከወደቁትና በቁም እያሉ ከተዘረፉት ማማዎች 756 ቶን ብረት መሰረቁን የተናገሩት ዳይሬክተሩ ይህም በገንዘብ ሲሰላ 72 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብር የሚገመት ኪሳራ ማድረሱን ገልጸዋል፡፡ የተሰረቀውን ብረት መልሶ ለመተካት ተቋሙ 23 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ማውጣቱንም አክለዋል፡፡

በዚህ የተነሳ በ2014 ዓ.ም በስርቆትና በመልሶ ግንባታ ተቋሙ እስከ መቶ ሚሊዮን ብር የሚደርስ ኪሳራ እንዳጋጠመው ተናግረዋል፡፡ የተቋሙ ኪሳራ ከአገልግሎት መቋረጥ ጋር ተያይዞ ይገኝ የነበረውን ገቢ ሳያካትት የተሰረቀውን ብረት እና ያንን ለመተካት የወጣውን ወጪ ብቻ ያካተተ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል፡፡

በስርቆቱ ምክንያት በተስተጓጎለው ሥራ 2ሺ 396 ሜጋ ዋት ሰዓት ኃይል የባከነ ሲሆን ይህም ወደ ገንዘብ ሲለወጥ አምስት ሚሊዮን ብር የሚደርስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ስርቆትን ለመከላከል ተቋሙ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን የተናገሩት አቶ ሞገስ ከኅብረተሰቡ ተወካዮች፣ ከጸጥታ እና ከፍትሕ አካላት ጋር ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል፡፡ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራው ውጤት እያስገኘ መምጣቱንና በአንዳንድ አካባቢዎች ወንጀለኞችን አጋልጦ ለሕግ እስከማቅረብ ተደርሷልም ብለዋል፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች በኅብረተሰቡና በባለድርሻ አካላት ትብብር ወንጀሉን ለመከላከል ቢሞከርም በሌሎች አካባቢዎች አሁንም ችግሩ መቀጠሉን ገልጸዋል፡፡ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ተከሰው በሚቀርቡ ወንጀለኞች ላይ የፍትሕ አካላት የሚጥሉት ቅጣት አስተማሪ አለመሆኑና ድርጊት ፈፃሚዎቹን ከጥፋታቸው እንዲታቀቡ የሚያደርግ አለመሆኑ ችግሩ ከአዙሪቱ እንዳይወጣ አድርጓል ብለዋል፡፡

ግብዓት ለማግኘት ሲሉ ስርቆቱን የሚደግፉና የሚረከቡ የብረታብረት ፋብሪካዎችና ባለሀብቶች እንቅስቃሴ ሊፈተሽ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መጥፎ ተግባር በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት የሚደረገውን ጥረት የሚያደናቅፍ በመሆኑ ፤ ኅብረተሰቡም ይሁን የሚመለከታቸው አካላት ጥፋተኞችን እንዲያጋልጡና የፍትሕ አካላትም በዚህ ወንጀል ተከሰው በሚቀርቡ ጥፋተኞች ላይ አስተማሪ ቅጣት እንዲጥሉ ዳይሬክተሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ማንኛውም ኃይል ለሰላም ተገዢ መሆን አለበት!

በተለይ በሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊት ላይ የተፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ የሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የትግራይ ሕዝብ እንደ አማራ እና አፋር ክልል ሕዝቦች ከፍ ያለ ጉዳትን አስተናግዷል። በዚህ መልኩ የሚገለጸው የትግራይ ክልል ሕዝብ ታዲያ፤ ከወር በፊት በደቡብ አፍሪካ ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በእጅጉ የገዘፈ ሰላምን እንደሚያገኝ ተስፋን ሰንቋል።

ይህ የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያውያን በተለይም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ለሚገኙት ለአማራ፣ አፋር እና ትግራይ ክልል ሕዝቦች፤ በዋናነት ደግሞ ለትግራይ ክልል ሕዝብ በእጅጉ አስፈላጊም፣ ትልቅ ተስፋ የተጣለበትም ነው። ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብ ከሃምሳ ዓመታት በተሻገረው የትግል ጉዞው፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቹን ገብሯል፤ በሺዎች የሚቆጠሩትም ለከፋ የአካል ጉዳት ተዳርገዋል፤ የበዙ እናቶችና አባቶች ያለ ጧሪ ቀርተዋል። እናም የትግራይ ሕዝብ አሁንም ድረስ ሞት፣ የአካል ጉዳትና ያለ ጧሪ መቅረት ከዳዋው አልወጣ ያለው ሲሆን፤ በተደጋጋሚ ባጋጠመው ጦርነትም ሰላም እንደ ሰማይ የራቀው ሕዝብ ሆኗል።

የትግራይ ሕዝብ ሰላም ብቻም አይደለም የናፈቀው፤ ኢኮኖሚያዊ እድገትም እንጂ። ምክንያቱም በትግራይ ክልል ከጦርነቱ በፊት ብቻ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ የክልሉ ሕዝቦች ለከፋ ድህነት በመጋለጣቸው የሴፍቲኔት ጥገኛ እንደነበሩ የሚታወቅ ነውና። በእንቅርት ጆሮ ደግፍ ላይ ሆኖበትም በጦርነቱ ምክንያት በርካቶች በመፈናቀላቸው እነዚህ ሕዝቦች ከፍ ላለ የሰብዓዊ ቀውስ እንዲዳረጉ ሆኗል። ለእለት ጉርሳቸው ሳይቀር የሰው እጅ ጠባቂ፣ የሰብዓዊ ድጋፍ ኃይሎችን ናፋቂ ሆነዋል።

የትግራይ ክልል ሕዝብ ከእነዚህ (ከነጻነት እና ኢኮኖሚያዊ ከፍታው) በላይ የናፈቀው ዐቢይ ጉዳይ የሁሉም መሰረት የሆነውን ሰላም ነው። ምክንያቱም ሕዝቡ መራብና መጠማቱ፣ እንዲሁም ጦርነት ካደረሱበት ጫና ጋር ተዳምሮ ለአያሌ ዓመታት በእጅጉ ተጎድቶ ኖሯል። የሰላም እጦቱ ከወንድም ሕዝቦች ጋር በሰላም ወጥቶ መግባት፣ በፍቅር አብሮ መኖር፣ በሃዘንና በደስታ አብሮ መቆምን የመሳሰሉ ማህበራዊም ሆኑ ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮቹን በእጅጉ ፈትነውበታል። ስለ ኢትዮጵያ ሞቶ፣ ስለ ኢትዮጵያውያን ነጻነት ዋጋ ከፍሎ ያለው ከሩ ሕዝብ በተደጋጋሚ ባጋጠሙት ጦርነቶች የሚፈልገውን ሰላም በሚገባ አለማጣጣሙ ያንገበግበዋል።

እናም ዛሬ ላይ የትግራይ ሕዝብ የቀደመ ማንነቱን መመለስ፤ የወንድማማችነት መሰረቱን ማጽናት፤ የመተጋገዝ እሴቱን ዳግም መትከል ይፈልጋል። በተቃራኒው የቂምና ቁርሾ መንገድ እንዲያበቃ፤ የጦርነትና የግጭት እሳቤ እንዲከስም ይሻል። ይህ እንዲሆን ደግሞ የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት እንዲፈጸም አብዝቶ ይመኛል። መመኘት ብቻም አይደለም ለተፈጻሚነቱ ሁሉም አካል ከልቡ ወስኖ እንዲሰራ ደጋግሞ ጠይቋል። ምክንያቱም የሰላም ስምምነቱ በቀዳሚነት የሁሉም መሰረት የሆነውን ሰላሙን የሚየጸናለት መሆኑን ያውቃልና። ከዚያም ከሰላሙ ባሻገር ያሉ ሰብዓዊና ቁሳዊ ፍላጎቶቹ እንዲሟሉለት እንደሚያደርግም ይገነዘባል።

ይህ የትግራይ ሕዝብ ምኞትና ፍላጎት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ፍላጎቱን ህልም አልያም እውን የማድረግ ትልቅ ኃላፊነት የተጣለባቸው በርካታ ባለድርሻዎች መኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም። ምክንያቱም የስምምነቱ ተግባራዊ መሆን ላይ በውስጥ ሕወሓት እና ከእርሱ ጋር ያሉ ኃይሎች፤ ከውጪ የሕወሓት ደጋፊዎችና የትግራይ ተወላጅ ዳያስፖራዎች በዚህ ረገድ መንግስት የጀመረውን ጥረት ከዳር እንዲደርስ የአጋዥነት ሚናቸውን መወጣት አለመወጣት ለውጤታማነቱ የራሱ አበርክቶ ይኖረዋልና። በዚህ ረገድ መንግስት ኃላፊነት እንደሚሰማው አካል ሰፊ ርቀት ተጉዟል፤ ህወሓትም እንደፈረመው የሰላም ስምምነት መልካም ጅማሮዎችን በመፈጸም ላይ ይገኛል።

ሆኖም ከዚህ በተቃራኒ የቆሙ ከሰላም ሳይሆን ከግጭት የሚያተርፉ፤ ለሕዝብ ሳይሆን ለራስና ቡድናቸው ጥቅም የቆሙ ኃይሎች በየቦታው መታየታቸው አልቀረም። ይሁን እንጂ ይሄን አይነት አዝማሚያና አካሄድ ለትግራይ ሕዝብ የሚፈይደው አንዳችም ነገር አይኖርም።

ምክንያቱም የትግራይ ሕዝብ ከሰላም እንጂ ከጦርነት አያተርፍም፤ ለሰለ እንጂ ለአፈና አልታገለም፤ ለብልጽግና እንጂ ለድህነትና ረሃብ ዋጋ አልከፈለም። ከኢትዮጵያውያን ወንድም እህቶቹ ጋር በፍቅርና በሰላም አብሮ ለመኖር እንጂ በጦርነት እየተዳማ ዘመኑን ለማሳለፍ አልተመኘም፤ አይመኝምም። በመሆኑም የትግራይ ሕዝብ ዛሬ ላይ አብዝቶ ለሚሻው ሰላም እውን መሆን ሁሉም ኃይል ለህዝቡ የሰላም ፍላጎት ተገዢ መሆን ይኖርበታል።


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አወዛጋቢው ምናባዊ ገንዘብ

### (ክሪፕቶ ከረንሲ)፤


**በቁምላቸው አበበ ይማም(ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com


**(የመጀመሪያ ክፍል)**

በሀገራችንም ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ሰው ምናባዊ ገንዘብን ወይም ክሪፕቶ ከረንሲን እንደሚጠቀም መረጃው እንዳለው ብሔራዊ ባንክ ባለፈው አመት ሚያዚያ ወር መጨረሻ ላይ በተለይ ለአዲስ ዘመን ገልጾ ፤ ኅብረተሰቡ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ ቢትኮይንና መሰል ምናባዊ ግብይቶች ላይ ከመሳተፍ እንዲቆጠብ ማስጠንቀቁ አይዘነጋም። አዲስ ዘመን ከዚያ በኋላም በተደጋጋሚ ዜጎች ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ በመወትወት ፋና ወጊ ስራ በመስራቱ በልኩ እውቅና ሊሰጠው ይገባል።

እኔም ክሪፕቶ ከረንሲ ምን ያህል ለአደጋ የተጋለጠና ብዙዎችን ለኪሳራ እየዳረገ መሆኑን በአብነት ለማነሳሳት እሞክራለሁ። ለመሆኑ ምናባዊ ገንዘብ ምንድን ነው? ቢቢሲ የእንግሊዘኛውን መዝገበ ቃላት ኦክስፎርድ ጠቅሶ፣ የገንዘብ ልውውጦችን ደህንነት የሚያረጋግጥ ፣ የተጨማሪ አሃዶች መፈጠርን የሚቆጣጠር እና ገንዘብ መተላለፉን የሚያረጋግጥ ጠንካራ ክራፕቶግራፊ የሚጠቀም መገበያያ እንዲሆን ተደርጎ የተቀረጸ ዲጂታል ገንዘብ ነው ሲል ይበይናል።

ብሔራዊ ባንክ ስለ ምናባዊ ገንዘብ በሚያስጠነቅቅ መግለጫው ፤ የኢትዮጵያ የገንዘብ መደብ ብር እንደሆነና በብሔራዊ ባንክ በሌላ አኳኋን ካልተፈቀደ በስተቀር በሀገሪቱ የሚከናወኑ ማናቸውም የገንዘብ ግንኙነቶች ሁሉ የሚከፈሉት በብር እንደሚሆን የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 በግልጽ እንደሚደነግግ አስታውሶ ፤ በኢትዮጵያ እንደ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ ቢትኮይን እና የመሳሰለው ምናባዊ ንብረትን (ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ) ለግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ኅብረተሰቡ ከእንደዚህ አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር ራሱን እንዲጠብቅ ባንኩ አሳስቧል ።

በክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 መሠረት በየትኛውም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድም ሆነ ሥርዓት ያለ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የገንዘብ ዝውውርም ሆነ ገንዘብ ነክ አገልግሎት መስጠት አይቻልም ያለው ባንኩ በመግለጫው ፤ በጥናት ለመረዳት እንደተቻለው በአሁኑ ወቅት ከሕግ እውቅና ውጪ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ እንደ ቢትኮይን እና የመሳሰሉት የምናባዊ ንብረት አገልግሎት በኢትዮጵያ እየተስፋፋ መጥቷል ብሏል ።

ብሔራዊ ባንክ ይሄን ማስጠንቀቂያ ካወጣ በኋላም የምናባዊ ገንዘብ ተጠቃሚው ቁጥር እያደገ መምጣቱን የሚያመላክቱ መረጃዎች እየወጡ ስለሆነ ለጥንቃቄ ይረዳ ዘንድ በአለማችን በሶስተኛነት ደረጃ ይገኝ የነበረ ምናባዊ መገበያያ ከሰሞኑን እንዴት እንደተንኮታኮተና ከዚያ በፊት ደግሞ የክሪፕቶ ንግስት ትባል የነበረች እንዴት የሚሊየኖችን ገንዘብ ሰርቃ እንደተሰወረች በቀጣይ አቀርባለሁ ።

ሞልቶ ተረፎ ከፈሰሰ ጾጋ በአንድ ሌሊት እንደ መንኮታኮት ያለ እንደ ከርቤና ሀሞት መራር ነገር የለም ይላል ባለፈው ወር ለንባብ የበቃው The Economist መጽሔት ። FTX EXCHANGE የዛሬውን አያድርገውና በአለማችን 3ኛው የክሪፕቶ ከረንሲ ግዙፍ ኩባንያ ነበር ። የ30 አመቱ የድርጅቱ መስራቹና ዋና ስራ አስፈጻሚው ሳም ባንክማን ፍሬድ ወይም በቅጽል ስሙ የክሪፕቶ ከረንሲ ንጉሥ ነገሥት ፤ የመጀመሪያው የዘርፉ ትሊኒየር ይሆናል ተብሎ ይጠበቅ የነበርና እንደ አርዓያ የሚታይ መሪ ነበር ይላል መጽሔቱ ።

ባለፈው አመት አጠቃላይ የክሪፕቶ ከረንሲ ኢንዱስትሪ ሀብት 800 ቢሊየን ዶላር ይገመት ነበር ዘንድሮ ግን ፤ ወደ 3 ትሪሊየን ዶላር ተተኩሶ ሰሞኑን በተፈጠረው ቀውስ የተነሳ መልሶ ወደ 830 ቢሊየን ዶላር አሽቆልቁላል ይላል ይኸው መጽሔት ። ወረተኛ የሆነውና አዲስ ነገር ከመሞከር ወደ ኋላ የማይለው ዘረ አዳም ፤ ከክሪፕቶ ከረንሲ ጋር እፍ ያለው ፍቅሩ ተግ በረድ ሳይልለት በአጭር ሊቀጭ ዋዜማው ላይ የደረሰ ይመስላል።

እንደ ክፍለ ዘመኑ ክስተት የሚቆጠረው የክሪፕቶ ከረንሲ አለም በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ1.3 ትሪሊየን ዶላር በላይ ከስሯል ። አስደንጋጩ የFTX ውድቀት የክሪፕቶ ከረንሲው ኢንዱስትሪ “Lehman Brothers”እንደ ማለት ነው ይላሉ ።የ2008 ዓም አለ ማቀፍ የፋይናንስ ቀውስ የተቀሰቀሰው “Lehman Brothers”በተባለው የኢንቨስትመንት ባንክ ብልሹ አሰራር ስለሆነ ።

ለሰሞነኛው የክሪፕቶ ከረሲ መንኮታኮት ዋነኛው መነሻ ምክንያትም የFTX EXCHANGE ነው ለማለት ነው ። የፌስቡኩ ማርክ ዙከርበርግ ፣ ጃክ ዶርሴ ፣ የአሜሪካ እግር ኳስ ኮከቡ ቶም ብራዲና የቀድሞ ባለቤቱ ጊሴሌ በFTX መክሰር በቢሊየን ዶላር የሚገመት አጥተዋል ። ከFTX ሽርክና የነበራቸው ሌሎች ዝነኞችን ጨምሮ የጡረተኞች ገንዘበ/funds/እና ታዋቂ ያልሆኑ በርካታ ቢለኒየሮችም ከስረዋል ። ታዋቂ ኢንቨስተሮችና ሰዎችን እያጠመደና እያግባባ ሽርክና እንደ ቼኮላት ሲቸበችብ የኖረው FTX በርካቶችን ጉድ ሰርቷል።

ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑ ኢትዮጵያውያንም አተርፍ ባይ አጉዳይ ሆነዋል። ከመንኮታኮቱ በፊት አጠቃላይ ሀብቱ 32 ቢሊዮን ዶላር ሲገመት የዛሬን አያድርገውና የ30 ዓመቱ የFTX መስራች ባንክማን ፍሬድ ወይም በቅጽል ስሙ የክሪፕቶ ከረንሲ ንጉሰ ነገስት ፤ እስካለፈው ወር ድረስ ባለብሩህ አእምሮ ፣ ለጋስና ተስፋ የሚጣልበት መሪ ተደርጎ ነበር የሚታየው ። ከጆርጆ ሶሮ ቀጥሎ ከዴሞክራት ፓርቲ ዋና ዋና ለጋሶች አንዱ ነበር ። የሚያሚ ሒት ሁለገብ ስታዲየም ፤ የ"FTX አሪና"ተብሎ እንዲሰየም 135 ሚሊየን ዶላር የከፈለ ሲሆን እንዲሁም ከበርክሌ የእግር ኳስ ስታዲየም ጋርም ለስያሜ 17.5 ሚሊየን ዶላር ከፍሏል ።

የሚገርመው ሁለገብ ስታዲየሙ የFTX መክሰረ እንደተሰማ "FTX ARENA"የሚለውን ቢል ቦርድ መብራት ለማጥፋት ጊዜ አልወሰደበትም ።ከታዋቂ ሰዎች የአሜሪካ ቅርጫት ኳስ ኮከቡና የ4 ጊዜ ሻምፒዎንና ስቲፍ ከሪ እና የግራውንድ ቴኒስ የ4 ጊዜ ግራንድ ስላም አሸናፊዋን ናኦሚ ኦሳካ፤ የቤዝ ቦል ኮከቡ ሾሄ ኦህታኒ ፤ የቀድሞው የከባድ ሚዛን ቡጤኛ ማይክ ታይሰን ፤የFTX አምባሳደሮች ቢሆኑም እንደ ሌሎች ዝነኞች ከፍተኛ ገንዘብ መክሰር አልቀረላቸውም ይላል የCNN ዘገባ ። ብራዲም ሌላው አምባሳደር ሲሆን የቀድሞ ባለቤቱ የFTX አማካሪ የነበረች ሲሆን ኢንቨስት ካደረጉት 650 ሚሊየን ዶላር ውስጥ በርከት ያለው ሳይከስር እንዳልቀረ ይነገራል ።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ከ5ኛው ገጽ የዞረ

## አወዛጋቢው ምናባዊ ...

FTX/Future Exchange/የተሰኘው ግዙፉ የክሪፕቶ ከረንሲ ወይም ቨርቹዋል ገንዘብ አልያም ምናባዊ ገንዘብ ሽርክና መስራችና ዋና ስራ አስፈጻሚ ሳም ባንክማን ፍሬድ ፤ የድርጅቱን ኪሳራ ተከትሎ ኃላፊነቱን በገዛ ፈቃዱ ከመልቀቁ ባሻገር መክሰሩንም ለመንግስት ማሳወቁን የቢቢሲው የሳይበር ዘጋቢ ገለጸ። ዘጋቢው ጆ ቲዲ ባንክማን ፍሬድ ከምናባዊ ገንዘብ ንጉስነት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወደ አግኝቶ ያጣ ተራ ዜጋነት ወረደ ይለናል ። ሰሞኑን The New York Times ባዘጋጀው አንድ መድረክ የቀረው ገንዘብ በመቶ ሺህ ብቻ የሚቆጠር መሆኑን ገልጿል። የኩባንያውን ፋይናንስ እንዴት ያንቀሳቅስና ያገላብጥ እንደነበረ በመንግስት ምርመራ ይጠብቀዋል። የአሜሪካ ሴኔትም ቃሉ እንዲሰጥ መጥሪያ ልኮለታል ።

ባለፉት ጥቂት አመታት የክሪፕቶ ከረንሲ ወይም የምናባዊ ገንዘብ ንጉሱንቃለ መጠይቅ ለማድረግ ሚዲ ያዎች ይሻሙት ነበር ። እሱም ባህማስ ከሚገኘው ቢሮው ሆኖ ስለ ስኬቱ ሚስጥርና ስለ ኩባንያው FTX ግዙፍነት አውርቶ አይጠግብም ነበር ይላል ቢቢሲ ። በአምስት አመታት ውስጥ እንዴት ቢሊየነር እንደሆነ እና ስለ ቀጣይ ርዕዩ ሲያወራ ሚዲያዎች አፋቸውን ከፍተው ያዳምጡ ነበር። በሁሉም ቃለ መጥይቆቹ ላይ ተደርቦ የሚሰማ የኮምፒውተር ማውዝ ክሊክ... ክሊክ... ክሊክ... የሚል ተከታታይ ድምጽ ይሰማል ። በቃለ መጠይቆች መሐል የባንክማን ፍሬድ አይን ደግሞ ኮምፒወተሩ ስክሪን ላይ ይንከራተታል።

በቲዊተር ገጹ እስኪነግረን ድረስ ቃለ መጠይቅ እያደረገ ጎን ለጎን ኮምፒውተሩ ላይ ምን እንደሚሰራ ግራ ተጋብተን ነበር ይላል የቢቢሲው ጆ ፤ በወርሀ የካቲት 2021 ዓም ከሚሊየን በላይ ተከታዩች ባሉት በቲዊተር ገጹ፤ " ቃለ መጠይቅ እያደረግሁና ስልክ እያወራሁ፤ የቪዲዮ ጌም መጫዎት እወዳለሁ።" በማለት ለብዙዎች ጋዜጠኞች ጥያቄ ሆኖ የኖረውን ነገር መለሰላቸው ። ለካ በዙም ቃለ መጠይቅ እያደረጉለት እያለ መልስ ይሰጣቸው የነበረ የቪዲዮ ጌም እየተጫወተ ነው ። "በቀን በቢሊየን ዶላር የሚቆጠር ሀብት የሚያገላብጡ ሁለት ታላላቅ ኩባንያዎችን መምራት ከሚፈጥርብኝ ድካም የማገግመው የቪዲዮ ጌም በመጫዎት ነው።"አለ። "ብዙዎች አልኮል አብዝቶ በመጠጣት ፤ ቁማር በመጫዎት ይዝናናሉ እኔ ደግሞ ጌም በመጫዎት ፈታ እላለሁ ።"በማለት አመሉን ይከላከላል ።

የቢቢሲው የሳይበር ዘጋቢ ጆ ቲዲ ስለ ክሪፕቶ ንጉሰ ነገስቱ የቪዲዮ ጌም ሱስ ማነሳሳቱን ቀጥሏል። የምናባዊ ገንዘብ ንጉሰ ነገስት ባንክማን ፍሬድ በተለይ"ስቶሪቡክ ብራውል"የተባለ የቪዲዮ ጌም ሱሰኛ ነው ይለናል ። የ30 አመቱ ባንክማን ፍሬድ ሀሳብ ውጤት የሆነው FTX የተሰኘ የክሪፕቶ ግዙፍ ሀብት ወይም ኢምፓየር ፤ በሳምንት ውስጥ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከተንኮታኮተ በኋላ የሚገራርሙ መረጃዎች እየወጡ ነው ። ሰሞኑን ግዙፉ ሴኩያ ካፒታል በጦማሩ ላይ ባስነበበው ዘገባ የክሪፕቶ ንጉሰ ነገስቱ ባንክማን ከትላልቅ የኢንቨስትመንት ቡድኑ ጋር በቪዲዩ ኮል ወሳኝ ስብሰባ እያደረገም ቪዲዮ ጌም ይጫወት ነበር ይለናል።

> የክሪፕቶ ንጉሰ ነግስቱ የሚከስሩ የክሪፕቶ ከረንሲ ኩባንያዎች በብዙ መቶ ሚሊየን ዶላር ወጭ በማድረግ ፤ ከኪሳራ በመታደግም ፤ የክሪፕቶ መድህን "Crypto's White Knight" እስከ መባል ደርሶ እንደነበር ቢቢሲ ያወሳል ። በዚህ ተግባሩ ግራ የተጋባው CNBC ባንክማን ፍሬድን ፤"የሚከስሮ ክሪፕቶዎችን ለምን ይህን ያህል ከፍተኛ ሀብት እያወጣህ ትታደጋለህ ፤"በማለት ሲጠይቀው ፤ "በሒደት ለክሪፕቶ ከረንሲ አለምም ሆነ ለደንበኞች ጥሩ ስለማይሆን ነው የምታደጋቸው ፤" ሲል ይመልሳል

ግዙፉ ሴኩያ FTX ላይ 210 ሚሊየን ዶላር ኢንቨስት አድርጎ የነበር ቢሆንም የንጉሰ ነገስቱን ክሪፕቶ መንኮታኮት ተከትሎ መክሰሩን ቢቢሲ ዘግቧል ። "የ32 ቢሊየን ኩባንያው FTX ድንገት ሲንኮታኮት ከሰረው ሴኩያ ብቻ አይደለም ።"ይላል የቢቢሲው የሳይበር ዘጋቢ ጆ ቲዲ ፤ 1.2 ሚሊየን ኩባንያዎች ፣ ታዋቂ ሰዎችና ግለሰቦች ጭምር ናቸው የከሰሩት። ኢንቨስት ያደረጉት ስለመመለሱም እርግጠኞች አይደሉም ።"ባንክማን ፍሬድ ራሱ በአጭር ጊዜ የሀብት ማማ ላይ በመውጣት መሰላል ተመልሶ ተፈጥፍጦ 16 ቢሊየን ዶላር ከስሯ። የክሪፕቶ ንጉሰ ነገስት በታዋቂው የማሳቹሴትስ የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ሒሳብና ፊዚክስ ማጥናቱን ቢቢሲ ያወሳል ።

ባለመጀመሪያ ዲግሪው ባንክማን ለስኬት አብቅቶት የነበረውን የንግድ ሀሳብ ያገኘው በዩኒቨርሲቲ ከመኝታ ክፍል ጓደኞቹ መሆኑን መለስ ብሎ ያስታውሳል ። በአገር አማን ከዚህ ቀውስ በፊት በዚያ ሰሞን ከቢቢሲ ሬዲዮ ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ FTX ለስኬት የበቃው ፤ " ከራስ ይልቅ የሌሎችን ተጠቃሚነት ማስቀደም፤"በሚለው መርሁ ነው በሚል ቢመጻደቅም እውነቱ ግን ለየቅል ነው ። ባንክማን ፍሬድ በቢቢሲ ልግጫውን ቀጥሏል ።"እንዴት ባለ ስራ ላይ ብስማራ ነው በብዙዎች ህይወት ላይ ተጽዕኖ የማመጣው ብዩ ብዙ ካወጣሁና ካወረድሁ በኋላ ነው ወደዚህ ስራ የገባሁ፤" ይላል ። የክሪፕቶ ንጉሰ ነገስቱ ከቢቢሲ ጋር ቀጥሏል ።

"ወደ ባንኪንግ ኢንዱስትሪው ዘርፍ የገባሁት ከፍተኛ ሀብት አፍርቼ መልሼ ለሕዝቡ ለመለገስ ነው። "ባንክማን የሽርክና ገብያ ማሻሻጥን የተማረው ኒው ዮርክ በሚገኝ ጄኒ ስትሬት በተባለ ኩባንያ ለአጭር ጊዜ በሰራበት ነው ። የቢትኮይን ክሪፕቶ ከረንሲ ዋጋ ሲዋዥቅ ያስተዋለው ንጉሰ ነገስቱ ዋጋው ሲወርድ ይገዛና ሲወደድ ደግሞ እየሸጠ ትርፍን ማጋበስ ተያያዘው ።

ለወራት ያህል ጠቀም ያለ ትርፍ ካገኘ በኋላ ከዩኒቨርሲቲ ጓደኞች ጋር በመሆን አላሜዳ ምርምር የተሰኘ የንግድ ድርጅት አቋቋመ ። ስራ እንደጀመርን ገንዘብ ከአንዱ ባንክ ወደ ሌላው ባንክና ከሀገር ወደ ሀገር ማስተላለፍ ተቸግረን ነበር ። ከሶስት ወር በኋላ ግን ቴክኖሎጂውም አግዞን ፤ የገንዘብ ዝውውሩን ማሳለጥ ቻልን ሲል ባንክማን ለአንድ ፓድካስት ያወሳል ። የክሪፕቶ ንጉሰ ነገስቱ ከአንድ አመት በፊት ለእነ ጃክስ ጆንስ ፓድካስት፤"ከፊታችን የሚገጥሙንን ፈተናዎችንና ማነቆዎችን በስኬት አለፍን ለዚህ ስኬት በቅተናል ። "ሲል ይገልጻል ። ቢቢሲም በ2018 ዓም በቀን አንድ ሚሊየን ዶላር ገቢ ያገኙ ነበር ሲል ወደ ኋላ መለስ ብሎ ያስታውሳል ።

በቅርቡ የCNBC የቢዝነስ ሪፓርተር ስለዚህ ስኬት ጠይቆት ነበር፤"ከአለሙት መድረስ እንከን የለሽ ያስመስላል ። በየዕለቱም ይገርመኝ ነበር ።"ይላል የክሪፕቶ ንጉሰ ነገስት ። ባንክማን ፍሬድ በ2021 ዓም በይፋ ቢሊየነር መሆኑ ይፋ ሆነ ይለናል ቢቢሲ ። FTX በቀን ከ10_15 ቢሊየን ዶላር በማገላበጥ 2ኛው ግዙፍ ክሪፕቶ ሆነ ። በተያዘው የነጮች አመት መግቢያ ላይ የFTX ሀብት 32 ቢሊየን ዶላር ተገምቶ ነበር ይለናል ቢቢሲ ፤ በአብዛኛው አሜሪካዊ ዘንድ ስሙ እንደ የቤተሰብ አባል ከመታወቁ ባሻገር ታዋቂው የቅርጫት ኳስ ሜዳ በስሙ እስከመሰየም ተደረሰ ።

እንደ ማት ዲመንና የተወዳጁ አሜሪካ ፉትቦል ኮከብ ቶም ብራዲ ያሉ ታዋቂ አሜሪካውያን ለFTX ድጋፋቸውን ገልጸዋል ። ሳም ባንክማን ለቲዊተር ተከታዮች የቀን ተቀን ህይወቱ ማጋራት ይወዳል ። ሲደክመው ቢሮው ውስጥ ባለ ክብ ሶፋ ላይ እንደሚተኛ ከፎቶ ጋር ይለጥፋል ። ሲያሻው በውድቅት ሌሊት ቲዊተር ላይ ይመጣና እንቅልፍ እምቢ ብሎኝ ወደ ቢሮዬ ተመልሻለሁ ይላል ። ለቪዲዮ ጌም ያለውን ሱስና እነዚህን የህይወት ቅንጣቶች ገጣጥሞ ለመረመረ ንጉሰ ነገስቱ አንዳች ችግር እንዳለበት መገመት ላይሳነው ይችላል ። ባንክማን ፍሬድ በልግስና አይታማም ይላል ቢቢሲ ። በመቶ ሚሊየን ዶላር የሚቆጠር ሀብት ለግብረ ሰናይ ድርጅቶችን ለግሷል ።

የክሪፕቶ ንጉሰ ነግስቱ የሚከስሩ የክሪፕቶ ከረንሲ ኩባንያዎች በብዙ መቶ ሚሊየን ዶላር ወጭ በማድረግ፤ ከኪሳራ በመታደግም ፤ የክሪፕቶ መድህን "Crypto's White Knight"እስከ መባል ደርሶ እንደነበር ቢቢሲ ያወሳል ። በዚህ ተግባሩ ግራ የተጋባው CNBC ባንክማን ፍሬድን ፤"የሚከስሮ ክሪፕቶዎችን ለምን ይህን ያህል ከፍተኛ ሀብት እያወጣህ ትታደጋለህ ፤"በማለት ሲጠይቀው ፤ "በሒደት ለክሪፕቶ ከረንሲ አለምም ሆነ ለደንበኞች ጥሩ ስለማይሆን ነው የምታደጋቸው ፤" ሲል ይመልሳል ። መች በዚህ ሊበቃው ንጉሰ ነገስቱ ፤"ለሚከስሩ ክሪፕቶ ከረንሲዎች መታደጊያ 2 ቢሊየን ዶላር በመጠባበቂያነት መመደቡን ፤"ገለጸ ። ነገ በእኔ እያለ የክሪፕቶ ከረንሲዎችን ሲታደግ እንዳልኖረ ፤ FTX ለከፍተኛ ኪሳራ ተዳርጎ ሲንኮታኮት ግን ማንም አልደረሰለትም ። በክፍል 2 የመጨረሻ መጣጥፌ የFTX ገመና እንዴት አደባባይ ላይ ሊውል እንደቻለና የሚሊየኖችን ሀብት ዘርፋ የውሃ ሽታ ስለሆነችው የክሪፕቶ ንግስት አስገራሚ ታሪክ አጋራችኋለሁ ።

ፈጣሪ የሀገራችንን ሰላም ያጽናልን !

አሜን ።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## በበይነ መረብ አስተዳደርና ተደራሽነት ላይ የቤት ሥራ የሰጠ ጉባኤ

ወርቅነሽ ደምሰው

ይህ ዘመን የቴክኖሎጂ እንደመሆኑ ዘመኑን የሚዋጅ ቴክኖሎጂን መጠቀምን የግድ ይላል። ዘመኑን የሚመጥን ቴክኖሎጂ መረጃን በመለዋወጥ ሥራን በቀላሉና በተቀላጠፈ መንገድ ማከናወን፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ሉዓላዊነትን ማስጠበቅ. ወዘተ ከማስቻሉም በላይ ለተወዳዳሪነት ወሳኙ መሣሪያ ነው። ቴክኖሎጂው የሚያመጣቸውን እድሎችና መልካም አጋጣሚዎችን መጠቀም ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ መሆኑም ይታመናል።

ከቴክኖሎጂዎቹ መካከል አንዱ የበይነ መረብ/ ኢንተርኔት/ ቴክኖሎጂ ነው፤ ዓለም አንድ መንደር መሆን ለቻለችበት ምክንያት አንዱ ምስጢርም ይሄው የበይነ መረብ ቴክኖሎጂ ነው። ያደጉትን ሀገሮች እድገት እያፋጠኑ ከሚገኙት መካከል አንዱ ይሄው ቴክኖሎጂ ሆኗል። ሌሎች በማደግና ላይ ያሉ ያላደጉ ሀገሮችም ይህን ቴክኖሎጂ በስፋት ለመጠቀም እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ታዳጊ ሀገራት ልማትን በማፋጠን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመሰለፍ የሚያደርጉትን ጥረት ለማሳካት በፍጥነት ቴክኖሎጂውን በመቀላቀል በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፍ የራሳቸውን እድገት ማፋጠን ይጠበቅባቸዋል።

በተለይ ዓለምን በእጅጉ እያስተሳሰረ ያለውን የበይነ መረብ (ኢንተርኔት) ቴክኖሎጂን በመጠቀም ልማትን፣ የንግድ እንቅስቃሴዎችን፣ ማኅበራዊ ጉዳዮችንና የሀገር ገጽታ ግንባታን በማቀላጠፍና ውጤታማ ማድረግ ለሀገር እድገት የላቀ አስተዋፅዖ ያበረክታል።

ኢትዮጵያም ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሰነቀችውን ራዕይ እውን የማድረግ ሩጫዋን ለሚያፋጥንላት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። መንግሥት የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት መሪ እቅድ የኢኮኖሚው አምስት ምሰሶዎች ብሎ ከያዛቸው መካከልም ይሄው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አንዱ ተደርጓል። ሀገሪቱ በሀገር ደረጃ ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት የሚያስችል እንዲሁም የቴክኖሎጂ ምህዳሩን ሊያፋጥን የሚያስችል የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን በመዘርጋት የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂንም እየተገበረች ትገኛለች።

የዲጂታል ዘርፉ በሀገራችን እያደገ መምጣቱ፣ የተለያዩ የዲጂታል ሥርዓቶች እየተገነቡ መሆናቸው፣ የዘርፉን ደህንነት ለማስጠበቅ ደግሞ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ያሉበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታሉ። በተለይ መንግሥት ለተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለመቀየር በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ስለመሆኑ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ሀገሪቱ ባለፈው ሳምንት ላስተናገደችው ዓለም አቀፉ የበይነ መረብ /ኢንተርኔት/ አስተዳደር ጉባኤ እንድትመረጥ ካስቻሏት ምክንያቶች መካከል ይሄው በዘርፉ እያካሄደች የምትገኘው ተግባር ነው። የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ ዓሊም ይህንኑ አመልክተዋል። ኢትዮጵያ በሳይንስና ቴክኖሎጂው ዘርፍ እያሳየች ያለችው ቁርጠኝነትና ለውጥ 17ኛውን ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ እንድታዘጋጅ ለመመረጥ አብቅቷታል ሲሉ ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ይህን ታላቅ መድረክ ነው እንግዲህ ባለፈው ሳምንት ለቀናት አካሂዳ በስኬት ያጠናቀቀችው። ኢትዮጵያ ይህንን ዕድል ልታገኝ የቻለችው በቴክኖሎጂ እያሳየች ያለችው እድገት እና የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ ፀድቆ ወደ ሥራ መግባቱ፣ የቴሌኮም ዘርፉን በዓለም ተወዳዳሪ እንዲሆን ክፍት ማድረጓ፤ ይህም ለቴክኖሎጂ እድገት ያላትን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑ ታምኖበት ነው።

ጉባኤው ታላቅ መድረክ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ጉባኤው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአስራ ስድስት ዓመት በፊት እ.ኤ.አ በ2005 ነው የተጀመረው። ባለቤት የሌለውን በይነ መረብ ለማስተዳደር ሀሳብ ለማፍለቅ የሚያስችል በየዓመቱ በአዘጋጅነት በተመረጡ ሀገራት የሚካሄድ ሲሆን፣ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ የበይነ መረብ ተጠቃሚነትን ተከትሎ የሚመጡ መልካም እድሎችና ተግዳሮቶችን በተመለከተ ተወያይቶ ምላሽ የሚሰጥ አካል ያስፈልገዋል በሚል ስምምነት እ.ኤ.አ በ2006 የመጀመሪያው ጉባኤም በግሪክ አቴንስ



በጉባኤው ላይ ከ3ሺ በላይ ተሳታፊዎችና ምሁራን ተገኝተዋል

ተካሂዷል። የዚህ ጉባኤ ዓላማ በዚህ ዘርፍ የተሠማሩ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ስለበይነ መረብ አስተዳደር ያሉ መልካም አጋጣሚዎች እና እድሎች እንዲሁም ፈተናዎችን በተመለከተ ሀሳብ የሚያንሸራሽሩበት እና የጋራ ግንዛቤ የሚፈጠሩበት ነው።

ይህ ጉባኤ አስገዳጅ ውሳኔዎች የሚወሰኑበት አይደለም፤ ውሳኔ አመንጪና ሰጪ የሆኑት የግሉን ዘርፍና መንግሥትን በጉዳዮቹ ላይ የመረጃና የፖሊሲ መነሻ ሀሳብ በመስጠት ጉዳዮች በሕግና በሌሎች ማዕቀፎች የሚፈቱበት አግባብ የሚመላከትበት ነው።

17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ ጉባኤም በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስተባባሪነት ከኅዳር 19 ጀምሮ እስከ 23 ቀን 2015 ዓ.ም ለአምስት ተከታታይ ቀናት በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የጉባኤ አዳራሽ ተካሂዷል። በጉባኤው የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ጸሐፊ አንቴኒዮ ፔድሮ ፣ የግል ማኅበራትን ጨምሮ ከሦስት ሺ በላይ ተሳታፊዎችና የዘርፉ ምሑራን ተገኝተዋል። በጉባኤው ላይም የኢትዮጵያና የአፍሪካ የኢንተርኔት ተጠቃሚነትን የተመለከቱ ጉዳዮች ጎላ ብለው ቀርበዋል።

በጉባኤው ላይ በይነ መረብ ለዓለም፣ ለአፍሪካና ለሀገሮች ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ የተጠቀሰ ሲሆን፣ ይህ ቁልፍ የልማት፣ የደህንነት፣ ወዘተ መሣሪያ ተደራሽ አለመሆኑ እንዲሁም በአስተዳደር በኩል በሚታዩ ክፍተቶች ለተለያዩ ችግሮች እየተጋለጠ ያለበት ሁኔታ ሰፊ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆነዋል። አካታችነትና የበይነ መረብ ደህንነት መወያያ ሆነዋል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በጉባኤው ላይ በዙም ባስተላለፉት መልዕክት በዓለም አቀፍ ደረጃ በበይነ መረብ ተደራሽነት ላይ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፤ አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት አንደሚያስፈልግም ነው ያስገነዘቡት።

ዋና ጸሐፊው፤ በዓለም 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ሕዝብ አሁንም ድረስ ከኢንተርኔት መገናኘት እንዳልቻለ ጠቅሰው፣ ከእዚህም ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የምትይዘው አፍሪካ መሆኗን አመልክተዋል። ‹‹እንደ አውሮፓ ባሉ አህጉራት ከ89 በመቶ በላይ ሕዝባቸውን የኢንተርኔት ተጠቃሚ አድርገዋል›› ያሉት ዋና ጸሐፊው፣ ‹‹ይህንን ስናስተውል አፍሪካና የአፍሪካ ሕዝቦች ወደኋላ የመውደቅ አደጋ ላይ ናቸው ማለት ነው›› ሲሉ ብለዋል።

እንደ ዋና ፀሐፊው ገለጻ፤ ለአፍሪካ ዘላቂ እድገት ኢንተርኔት ጉልህ ሚና ይጫወታል ። ስለዚህ ለአፍሪካ የወደፊት ዲጂታል ጉዞ እውን መሆን ከጉባኤው ብዙ ይጠበቃል።

በርግጥ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ አገራት ዲጂታል ቴክኖሎጂ የመጣው እድል ለመጠቀም እየሠሩ ናቸው። ዜጎቻቸውን በቴክኖሎጂ አካታች ለማድረግ ጥረቶች ያደርጋሉ። ኢንተርኔት ለዜጎች ለማዳረስ ጥረት ያደርጋሉ። ያም ሆኖ ግን በአፍሪካ ኢንተርኔት የሚጠቀመው ከሦስት ሰው አንዱ ነው። ይህ ማለት ወደ 871 ሚሊዮን ዜጎች ከበይነ መረብ ግንኙነት ውጭ ናቸው ማለት ነው። ይህም አስተማማኝ የበይነ መረብ ዝርጋታን በዓለም ላይ ለማዳረስ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ ያመለክታል። ይህን ሕዝብ ተጠቃሚ ማድረግ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ የበይነ መረብ ግንኙነት ለሁሉም እንደሚያስፈልግ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ አስገንዝበዋል። አስተማማኝ የበይነ መረብ ዝርጋታን በዓለም ላይ ለማዳረስ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ አመልክተው፤ በተለይ ለአፍሪካ አስተማማኝና አካታች የዲጂታል ደህንነት መተግበር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል። ሦስት ቢሊዮን የዓለም ሕዝብን የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

ሁሉን አቀፍ አህጉራዊ ብልጽግናንና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በትብብር መሥራት እንደሚገባም ነው ዋና ጸሐፊው ያመለከቱት። ሁሉን አቀፍ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማሳካት መረባረብ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ምክትል ዋና ጸሐፊ ሊ ጁንሁዋ እንደገለጹት፤ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ የበይነ መረብ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ኢንቨስትመንትን፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታን በማሳደግ ትስስር ሊፈጥር ይገባል። በተለይም እንደ አፍሪካ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በዘርፉ በትኩረት መሥራት ይኖርባቸዋል።

የበይነ መረብ ተደራሽነትን ለማስፋት ዘርፉ በፖሊሲ መደገፍ አለበት ያሉት ሊ ጁንሁዋ ፣ መንግሥታት ለዘርፉ የሚሰጡት ትኩረት፣ ዘርፉን በረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት መደገፍና የዲጂታል ዘርፉ ክህሎትን ማሳደግ የበይነ መረብ ተደራሽነትን ለማስፋት ወሳኝ ጉዳዮች በመሆናቸው ትኩረት ሊደረግባቸው እንደሚገባ ገልጸዋል።

የዲጂታል አብዮት እየተጀመረ ያለባት አፍሪካ ግልጽና አካታች ስትራቴጂን በመንደፍ ልትሠራ እንደሚገባትም አስገንዝበዋል። መንግሥታት ለዘርፉ የሚሰጡት ትኩረት፣ ዘርፉን በረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት መደገፍና የዲጂታል ዘርፉ ክህሎትን ማሳደግ የበይነ መረብ ተደራሽነትን ለማስፋት ወሳኝ ጉዳዮች መሆናቸውን አንስተዋል፡፡

በመድረኩ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በበኩላቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ የበይነ መረብ ተደራሽነትን በማስፋፋትና የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ በርካታ ሥራዎችን እየሠራች ትገኛለች። በዚህ ሂደት ላይም ዘርፉ ለብልጽግና ጉዞዋ የሚፈጥርላትን መልካም ዕድል እንደ አዳጊ ሀገር እውቅና ትሰጣለች።

ኢትዮጵያ በዲጂታል ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ዘርፍ ፈጣን ለውጥ እያመጣች መሆኑን ጠቅሰው፤ የበይነ መረብ አገልግሎት የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተያዘውን የአሥር ዓመት እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖረውን ፋይዳም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2017 የነበረው 19 ሚሊዮን የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር በ2022 ወደ 30 ሚሊዮን ከፍ ብሏል፤ የ4ጂ ኔትወርክ ሕዝብ በሚበዛባቸው ከተሞች እና 5ጂ ኔትወርክን በትላልቅ ከተሞች መዘርጋቱ ግንኙነቱን እያፋጠነ ይገኛል። በመላ ሀገሪቱ 2 ሺህ300 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የኢንተርኔት አገልግሎት አላቸው።

‹‹በዘመነ ዲጂታል የበይነ መረብ ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህም በትራንስፖርት፣ በግብርና እንዲሁም በጤና እድገት ላይ ዘርፉ ያለውን አወንታዊ ድጋፍም አመላክተዋል። ኢትዮጵያ በኮቪድና በሌሎች ሰው ሠራሽ ችግሮች በተፈተነችበት ወቅት ሥራን በበይነመረብ ማካሄድ መቻሏን አዳዲስ ፈጠራዎች እንዲበረታቱ ማድረጉንም በመልካም ጎኑ አንስተውታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩም አፍሪካ ደህንነቱ የተጠበቀ የበይነመረብ አስተዳደር ሊኖራት ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል። የበይነ መረብ አስተዳደር በጠንካራ ፖሊሲ መደገፍ እንደሚገባውም ነው የጠቆሙት። ያለፉት አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ የፈተናም የዕድልም ዓመታት ነበሩ ሲሉ ጠቅሰዋል። በይነ መረብ በርካታ በጎ ነገሮች ቢኖሩትም የተዛባ የመረጃ ስርጭትን በማስፋፋት ረገድም አሉታዊ አስተዋፅኦ አለው ብለዋል። ዘርፉ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማሰራጨት ሀገሪቷን ሲጎዳ መክረሙንም በአብነት ጠቅሰዋል።

ከሁለት ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ወደ አካታች ዲጂታል ኢኮኖሚ በምታደርገው ጉዞ አንድ ወጥ የሆነ ራዕይ ያስቀመጠ ብሔራዊ ዲጂታል ስትራቴጂ በሥራ ላይ ማዋሏን የጠቆሙት ዶክተር ዐቢይ፣ ስትራቴጂው መሠረተ ልማትን ማጎልበት፣ ሥርዓቶችን ማስቻል፣ ዲጂታል መድረኮችን እና የዲጂታል ሥነ-ምሕዳርን በመገንባት ላይ ያተኩራል ብለዋል።

ለዚህም ደህንነትን እና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት መንግሥት ብሔራዊ የሳይበር ደህንነት ተቋማትን ለማጠናከር የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። እነዚህ ተቋማት የአገሪቱን የሳይበር ምሕዳር ከመጠበቅ በተጨማሪ በተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የዜጎችን ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ በመሥራት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

በጉባኤው መጠናቀቂያ ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በጉባኤው የተነሱ ነጥቦች በበይነ መረብ አስተዳደር የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያስችሉ መሆናቸውን ተናግረዋል። በበይነ መረብ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ሊኖር እንደሚገባም ጉባኤው ማመላከቱን ጠቅሰዋል። የተነሱት ሀሳቦች ለሁሉም ሀገሮች ጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሁሪያ ዓሊ በጉባኤው ከ170 በላይ አገሮች መሳተፋቸውን ጠቅሰው፣ በተለይም ያልተቆራረጠ የኢንተርኔት ተደራሽነት እንዲኖር በርካታ ሀሳቦች መንሸራሸራቸውን ገልጸዋል። ከ2ነጥብ 7 ቢሊዮን በላይ ከኢንተርኔት ውጭ የሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ መሥራት እንደሚገባ የቤት ሥራ የተሰጠበት ነው ሲሉ አስገንዝበዋል።

የኢንተርኔት አባት በመባል የሚታወቁት ቬንት ሰርፍ ኢትዮጵያ ጉባኤውን በሚገባ ማስተናገዷን አስታውቀዋል፡ ፡በመድረኩ የተገኙት ሀሳቦች በኢንተርኔት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ ለሚሠሩ ሥራዎች ትልቅ ግብዓት የተገኘበት ሲሉም ጉባኤውን ገልጸውታል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት በዕድሎችና ፈተናዎች መካከል

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፣ ከኢኮኖሚ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ከህዝብ እንደራሴዎች ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተዋል። በተለይም የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታችን ምን ይመስላል? ዕድገታችን በንግግሩ አልተመላከተም፤ የዘንድሮ ዓመት የዕድገት ዕቅዳችን ፤ የባለፈው ዕድገታችንስ ምን ያህል ነው? የሚል እና መሰል ጥያቄዎች ተነስተውላቸው ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያም ኢኮኖሚ በቀላሉ የማይሰበር (ረዚሊያንት) መሆኑን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የተጀመረው ዕድገት መቀጠል የሚችል መሆኑን ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ይህንን ጉዳይ የሚገመግሙ ሰዎችን ግራ እስኪያጋባቸው ድረስ ኢኮኖሚው ያጋጠመውን ፈተና ተቋቁሞ መሻገር ችሏል። ጫና ተቋቁሞ መሻገር ችሏል ሲባል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በ2014 የበጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 6 ነጥብ 16 ትሪሊዮን ደርሷል። ይህም ማለት በዶላር ሲሰላ 126 ነጥብ 7 ቢሊየን ዶላር ማለት ነው ሲሉ አብራርተዋል። የነፍስ ወከፍ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሺህ 212 ዶላር ደርሷል። ይህ ብቻ ሳይሆን ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛው ግዙፉ ኢኮኖሚ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ሆኗል ብለዋል።

ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገራት ሶስተኛው ግዙፍ ኢኮኖሚ የኢትዮጵያ ሆኗል። ይህ ዳታ የመንግስታችን ዳታ አይደለም። የዓለም ባንክ ዳታ ነው። የዓለም ባንክ ዘንድሮ ባደረገው ግምገማ ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛው ኢኮኖሚ ተበልጦ የነበረውን አስተካክሎ፤ ከሰሃራ በታች ሶስተኛው ግዙፉ ኢኮኖሚ መሆን ችሏል ሲሉ ነበር ያብራሩት።

ኢንዱስትሪም ዘንድሮ አራት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል ሲሉ የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢንዱስትሪ ከአምናው በተወሰነ ደረጃ ቅናሽ አሳይቷል ብለዋል። ቅናሽ ያሳየበት ምክንያት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከሲሚንቶ ጋር ተያይዞ ያለው ዕድገት ያዝ የተደረገ እንደሆነ ጠቅሰው፤ እንደአምናው ስላልሆነ አጠቃላይ በኢንዱስትሪው ላይ ያሳደረው ጫና ቢኖርም በማኑፋክቸሪንግ ግን ጥሩ ውጤት ተገኝቷል ማለታቸው ይታወሳል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላለፉት ዓመታት በተለይም ባለፈው ዓመት በርከት ያሉ ሰው ሰራሽ ፈተናዎች እና አደጋዎች ገጥመውት ነበር። ከፍተኛ ፈተና ከነበሩት ውስጥም ጦርነት በአገር ውስጥም በውጪም መሆኑ ነው፤ የዩክሬን እና የራሺያ ጦርነት በዓለም ደረጃ የፈጠረው ጫና እንዲሁም ድርቅ ኮረናን ጨምሮ በኢኮኖሚው ላይ በስፋት ዱቀሳ ያሳረፉበት ዓመት ነበር ማለት ይቻላል።

የተለያዩ ምሁራን በኢኮኖሚ እድገቱ ዕድሎች እና ፈተናዎች ዙሪያ ያላቸው አተያይ ምን ይሆን ስንል አነጋግረናቸዋል። ዶክተር ዓደም ፈቶ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ተመራማሪ ናቸው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር በግርድፉ ብቻ ወስዶ እድገት አለ ወይንም የለም የሚል መከራከሪያ ከማቅረብ ማሳያዎችን መጥቀስ አግባብ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

‹‹የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላለፉት ዓመታት በተለይም ባለፈው ዓመት በርከት ያሉ ሰው ሰራሽ ፈተናዎች እና አደጋዎች ገጥመውት ነበር። ከፍተኛ ፈተና ስለነበረ፤ ጦርነት በአገር ውስጥም በውጪም የዩክሬን እና የራሺያ ጦርነት በዓለም ደረጃ የፈጠረው ጫና እንዲሁም ድርቅና ኮረና ያመጡት ጫናዎች መኖራቸውና ይህም በስፋት በኢኮኖሚው ላይ ጫና ያሳረፈበት ዓመት ነበር መባሉን ይስማሙበታል።



ዶክተር አደፍርስ ወርቁ



ዶክተር አደም ፈቶ

እንደ ዶክተር ዓደም ገለፃ ፤ ታዲያ ይህን ሁሉ ጫና ተቋቁሞ የቀጠለ ኢኮኖሚ አድጓል ለማለት ማሳያ አለ ባይ ናቸው። ነገር ግን ዕድገቱ የተመሰረተበትን መንገድ አይቀበሉትም። በአሁኑ ወቅት 80 ከመቶ የሰው ሃይል የተሰማራው በግብርና ነው። ወደ ውጭ የሚላከው ምርትም ዋነኛ ምንጩ ግብርና ነው። ይህም ኢኮኖሚውን ጠንካራ አድርጎታል። ይህ ባይሆን ኖሮ ኢኮኖሚው መውደቁ አይቀሬ ነው። ኢትዮጵያ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሃይል ብዙ አቅም አሏት። ይህም ቢሆን ግን የሚያኩራራ አይደለም። ብዙ የመልማት ፀጋዎች ያሏት ሀገር ናት፤ ይህ ጸጋ ለወደፊትም የሚጠቅም ነው ይላሉ።

‹‹የባለፈው ዓመት የጂዲፒ እድገት ስድስት ነጥብ አራት በመቶ ነው የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህ ዓመት ያለን ዕቅድ ቢያነስ ሰባት ነጥብ አምስት ነው። በተለይ አሁን የተፈጠረው የሰላም ሁኔታ ማስጠበቅ ከቻልን ቢያንስ ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ እናድጋለን ብለን እናስባለን። የባለፈው ዓመት ስድስት ነጥብ አራት ዕድገት የተረጋገጠው ቀደም ሲል እንዳነሳችሁት ብዝሃ ዘርፍ፣ ብዝሃ ተዋናኝ መሆን አለበት። ኢኮኖሚያችን፤ ግብርና መር፣ ኢንዱስትሪ መር እያልን በተወሰነ ሴክተር መታቀብ የለብንም፤ ሰፋ ያሉ የልማት ዘርፎችን እንደዋና መንቀሳቀሻ አድርገን ብንሰራባቸው አቅሞች ስላሉ ሊወጡ ይችላሉ›› ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግብርና መዘመን እንዳለበት መጠቆማቸውም ይታወሳል፤ የኢኮኖሚ ምሁሩም በዚሁ ሃሳብ ይስማማሉ።

እንደ ዶክተሩ ማብራሪያ፤ ይህ አካሄድ መልካም ቢሆንም ማክሮ ኢኮኖሚው ብዙ ጉድለቶች አሉበት ባይ ናቸው። ከፍተኛ የዋጋ ንረት አለ። ምግብ ነክ ላይ 42 ከመቶ የሚደርስ ግሽበት አለ። ይህም ከዓለም አቀፍ መስፈርት ሁለት እጥፍ ነው። በገንዘብ የውጭ ብድር ጫናው በጣም ከፍ ያለ ነው፤ ይህም በእጅጉ ኢትዮጵያን ሊያሳስብ የሚገባ ነው። የመንግስት በጀት ጉድለት ያለበት ሲሆን ወጪና ገቢ የማይመጣጠን ነው። የወጪ እና ገቢ ንግድም ልዩነት ያለ ሲሆን፤ በአሃዝ 10 ቢሊዮን ዶላር ደርሷል። የውጭ ሀገር ገንዘብ ክምችትም ከአንድ ወር በታች የሆነ የገቢ ንግድ ለመሸፈን የሚውል በመሆኑ አደገኛ አካሄድ ላይ ነው።

ሥራ አጥነቱም 21 ከመቶ የደረሰ ሲሆን በትልቅ ከተሞቹ አሃዙ ወደ 30 በመቶ ደርሷል የሚሉት ዶክተር ዓደም፤ ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ትልቅ መዋቅራዊ ችግር ያለባት ሀገር ናት ብለዋል። እስካሁንም ከበሬ እርሻ ሳይዘል የተንጠለጠለውም በእርሻ እና አገልግሎት ላይ ብቻ ነው። ይህም ወደ ተሻለ መሸጋገርና ኢንዱስትሪውን ማዘመን እንደሚገባ ያመላክታል ሲሉ ያብራራሉ።

**ኢትዮጵያም ከዓለም ከቀዳሚዎቹ 25 ትልቅ ብዝሃ ህይወት ካሳቸው ሀገራት አንዷ ስትሆን፤ ከአፍሪካ ደግሞ ከቀዳሚዎቹ አምስት ተርታ ያሰልፋታል**

በ10 ዓመት ማክሮ ኢኮኖሚ እቅዱም በጣም የሚበረታታ ሃሳብ ቢሆንም፤ የሀገሪቱ ማክሮ ኢኮኖሚ ከፍተኛ የሆነ አለመመጣጠን ይታይበታል። መዋቅሩም ማነቆ ያለበት ነው። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ጠንካራ ቢሆንም፤ ብዙ ጉድለቶች አሉበት። ነገር ግን እነዚህን ማነቆዎች መፍታት ከተቻለ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቅ የማደግ ተስፋ አለው። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከግብርና ወደ አገልግሎት እየተሸጋገረ ስለሆነ ይህን በፍጥነት የማረምና ወደ ኢንዱስትሪውም የሚዞርበትን ምዕራፍ ማበጀት ይገባል። እነዚህና መሰል ችግሮች ከተስተካከሉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ያድጋል። የህዝቡን የዲጅታል እውቀት ማጎልበትም ምጣኔ ሃብቱን ለማሳደግ የጎላ ሚና አለው ይላሉ።

በኢትዮጵያ ደን ልማት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር አደፍርስ ወርቁ በበኩላቸው፤ ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ አረንጓዴ አሻራ ሌጋሲ የማስቀጠል ስራዎች መሰራታቸውን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረው አንድምታ በእጅጉ የላቀ መሆኑን ይናገራሉ። ችግኝ ከመትከል በላይ የተገኘው ውጤት በቁጥር ብቻ የማይገለፅ መሆኑን በመጥቀስም፤ የመሬት መጎሳቀልን በመጠበቅ ምርታማነት መጨመሩን ያብራራሉ። የአየር ንብረት መጋለጥን በመጠበቅ፤ የውሃ ሃብት መንከባከብና ሌሎች ፋይዳዎችን የሚሰጥ በመሆኑ የደን ኢንዱስትሪውን መልስ የሚሰጡ ሥራዎች ናቸው። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ ከውጭ በሚሊዮኖች ዶላር የምታወጣውን ወጪ የቀነሰ ሲሆን፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በእጅጉ የሚያሳድግና፤ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ማደግን የሚያሳይ ነው። በአንድ ችግኝ ጣቢያ ለ10 ሰዎች የሥራ እድል የተፈጠረ ሲሆን በመላ ሀገሪቱ 121 ሺ የችግኝ ማፊያ ጣቢያዎች አሉ። በዚህም ተፈጠረው የሥራ ዕድል ወደ ሀገሪቱ ጠቅላላ ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚገባ እና በትልቁ በማክሮ ኢኮኖሚ የሚሰላ መሆኑን ያብራራሉ።

በዓመት 92 ሺ ሄክታር ደን ይመነጥር እንደነበር የገለጹት ዶክተሩ፣ ይህም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረው ጫና በቀላሉ የሚገመት አይደለም። በአንድ ሀገር የማክሮም ሆነ የማይክሮ ኢኮኖሚ አካሄድና ዕድገት የሚመጋገብና የሚናበብ መሆን አለበት። የአረንጓዴ ልማት በማክሮ ኢኮኖሚ ላይ የሚጨምረው የራሱ የሆነ ትልቅ ትርጉም አለው ። በጠቅላላው ሲታይ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትን ብቻ እያስመዘገበ ሳይሆን ዓለም እየተጨነቀችበት ያለውን የአየር ብክለትን በመከላከል ቀዳሚዋ ከመሆን በተጨማሪ አረንጓዴ ልማትና እድገትን ያረጋገጠ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያም ከዓለም ከቀዳሚዎቹ 25 ትልቅ ብዝሃ ህይወት ካላቸው ሀገራት አንዷ ስትሆን፤ ከአፍሪካ ደግሞ ከቀዳሚዎቹ አምስት ተርታ ያሰልፋታል። ይህም በድምር ውጤት ሲታይ የሀገሪቱን ዕድገት በጽኑ የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ ይጠቅሳሉ። ማክሮ ኢኮኖሚና የሀገር እድገት ከአረንጓዴ ልማት ጋር የማይነጣጠሉ ስለመሆናቸው ይጠቁማሉ። በዚህም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር እነዚህን ታሳቢ ያደረገ ስለመሆኑም ያስረዳሉ።

ምሁራኑ እንደሚስማሙት፤ ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ ሃብት ከተጠቀመች እና አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት ረገድ የያዘቻውን ግብ ካጠናከረች እንዲሁም በዓለም አቀፍ መመዘኛ መሰረታዊ የሚባሉ ችግሮችን ካስተካከለች በቅርቡ ዕድገቷን ታረጋግጣለች የሚል እምነት አላቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በበኩላቸው፤ የብልፅግና ፍላጎት በአፍሪካ ገዘፍ ካሉ ኢኮኖሚዎች ውስጥ አንዱ ማድረግ አለብን ብለዋል። ፈተናዎችም ይበልጥ እንድንሰራ፤ እንዳንተኛ አግዞናል። የራሱ ስብራት ቢኖረውም፤ ተጠናክሮ ለመስራት ግን ዕድል ፈጥሯል የሚል የፀና እምነት አለኝ ሲሉ የምጣኔ ሃብት እድገት ላይ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል።

ምሁራኑ የሚስማሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ሀሳብ ዙሪያ ነው። በሀገራችን ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የሚያስችል ሰፊ ዕድል አለ። ሆኖም እድገቱን የሚገዳደር ደግሞ ፈተና አለ ። የሚያጋጥሙ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎችን ተቋቁሞ ውጤታማ በሚያደርጉ ስራዎች ላይ ጉልበት ጨምሮ መስራት ከተቻለ ያልታዩ የልማት አማራጭ ዘርፎችን ማየትና ማስፋት ከተቻለ የሚታሰበው ዕድገትን ማረጋገጥ ይቻላል የሚል ትንበያ አላቸው።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ወጣቷ የልብ ስብራቷን የጠገነችበት ጥንካሬ

**ሰላማዊት ውቤ**

አዳማ አያቴ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ኖሬያለሁ። ትምህርቴንም እዛው የመከታተል አጋጣሚውም ነበረኝ። ከከተማዋ ከወጣሁ በኋላም ቢሆን ቅዳሜና እሁድ ጨምሮ ትምህርት በማይኖረኝ ሰዓት እየሄድኩ ጊዜን አሳልፍ ነበር።

በዚህ አጋጣሚ አያቴ ጊቢ ካሉት ተከራዮች አንዱ ከሆነው ከባጃጅ አሽከርካሪው ጋሻውና ከቤተሰቡ ጋር ተዋውቀናል። ቤተኞች ነን ማለት ይቻላል።በተለይ ከሚስቱ ጋር በጣም እንግባባ ነበር።ስትወልድ ከማረስ ጀምሮ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶችም ላይ አብረን ነበርን። እኔም ጋሻውን እንደ ታላቅ ወንድሜ አየው ነበር።እሱ ጋር የሚመጣና አጎቴ የሚለው አንድ ዕድሜው 60 ዓመት የሚጠጋ ታምራት የሚባል ሰውዬንም በእሱ አማካኝነት ተዋወቅሁ። ከአያቴ ጋርም ከአይን ያለፈ ትውውቅ ባይኖራቸውም ታውቀዋለች። ሰውዬው በአዳማ ከተማ ጋራዥ ያለውና የታወቀ ሀብታም ነበር። ከዚህም በላይ ልጁ የታወቀችና የተዋጣላት ተዋናይ ስለነበረች ከሀብቱ በተጨማሪ በአርቲስቷ ልጁም ጭምር ይታወቅና ይከበራል።

“ታድያ አንድ እሁድ እንደተለመደው አዳማ ሄጄ ነበር። ተከራዩ ጋሻው ነይ ዘወር ዘወር ብለን እንምጣ አለኝ።መለስ ብዬ ወደ አያቴ ቤት በመግባት ሳሎን ቁጭ ብላ ለነበረችው እናቴ መጣሁ ዞር ዞር ብዬ በማለት ነገርኳትና ባጃጅ ውስጥ ገባሁና ቁጭ አልኩ።ተሳፋሪ እየጠበቀ ምን አለ ታምራት ቢደውልልኝና ልጋብዝህ ቢለኝ አለ።ወድያው ስልኩ ጮኸ። ታምራት ነው ብሎ አነሳው። የልጁ ድምፅ እንጂ የሰውዬው ባይሰማኝም አወሩ። ህንደኬም አለች ሲለው ሰምቻለሁ። ሰውዬው ያለበት ቦታ ሄድን።መጠጥ ይዘው ቁጭ ያሉ ብዙ ሰዎች ያሉበት ነበርና ደስ እንዳላለኝ አይተው ቤት እንቀይር አሉና ወጣን።ከዚህ ቀደም ባጃጅ እንዳለው ጋሻው ሲያወራ ባልሰማም ሰውዬው ባጃጅ ይዞ ነበርና በእሱ ባጃጅ ለጾም መያዥያ ሊገባበዙ ወደ ተስማሙበት ሆቴል አመራን” ትላለች።

ሆቴል ከገቡ በኋላ የአያቷ ተከራይ ጋሻው መፀዳጃ ቤት ደርሼ ልምጣ ብሎ ሄደ።አቶ ታምራትም ህንደኬን ቁጭ አድርጎ ምግብ ልዘዝ ብሎ ተነሳ።ሁለቱም ቆየት ብለው ተመለሱ። ጋሻው ስፕራይት እንጂ ሌላ የአልኮል መጠጥ ጠጥታ እንደማታውቅ ቢያውቅም የሚጠጣ ቀይሪ ማለቱ ግን አልቀረም።

ህንደኬ ትናገራለች “ የሚጠጣ ልቀይር ብዬ ቶኒክ አልኩ። ቶኒክ መጠጥ ቁጭ ብሎ ነበር። ከፍቼ ልጠጣ ስል ታምራት ሳትበይ አትጠጪ ከበላሽ በኋላ ጠገብኩ ብለሽ ንገሪኝና ትጠጫለሽ አለኝ። የታዘዘው ምግብ እስኪመጣ ስለ ታዋቂዋ ልጁ ማውራት ጀመሩ።ጋሻው ወጣት ልጁ አባቷን እንደ አምላኳ እንደምታየውና ከፈለኩ ውጪ መሄድ እንደምችል ምናምን ሲያወሩ ቆዩ። ወድያው ምግቡ መጣና እጄን ልታጠብ ስነሳ ጋሻውን ይዘሃት ሂድ አለው።ታጥቤ ስመጣ ቶኒኩ ተቀድቶ ነበር የጠበቀኝ።በልቼ ስጨርስ አሁን ጠግቤአለሁ ልጠጣ አልኩና ከተቀዳው ቶኒክ የተወሰነ ተጎነጨሁ”።

በወቅቱ የጠጣችው ቶኒክ ከምታውቀው ጣዕም የተቀየረ ስለመሰላት ብዙ መጠጣት አልቻለችም፤ ወዲያው ታምራት ከቀረበው ምግብ ቢያጎርሳትም እሱም ሳይጥማት ቀረና ተወችው። ከዚህ በኋላ ግን ህንደኬ የሆነውን ነገር ማስታወስ አትችልም፡

“ በወቅቱ ራሴን ስለሳትኩ የሆነውን አላስታውስም።ወደ አልጋ እንዴት እንደተወሰድኩ የማውቀው ነገር የለም።ራቁቴን ከአልጋ ላይ ያገኘሁት እኩለ ሌሊት ላይ ነው።አስገድዶ መድፈር ተፈፅሞብኝ ነበር።በዚህ የተነሳ ከፍተኛ ህመም እየተሰማኝ ነው።ሰውነቴ ደክሞ ከአልጋው ላይ መነሳት ሁሉ ተስኖኝ ነበር” በማለት ከደነዘዘችበት ስትነቃ የገጠማትን ትናገራለች።

አሁን እኩለ ሌሊት ነው ክፍሉን ስታየው አታውቀውም። ራሷን ስታይም ራቁቷን ናት ቀን ከጋሻው ጋር ስትገናኝ የለበሰቻቸው ልብሶች መሬት ላይ ተዝረክርከዋል። የታምራት ልብሶች ግን ወንበር ላይ በክብር ተቀምጠው ነበር። ታምራት ደግሞ ከጎኗ ተኝቷል።እሷ ግን አልጋው ላይ መተኛት ቀርቶ መቀመጥ በጣም ነበር የቀፈፋት። ከአልጋው እንደምንም ወርዳ ሱሪዋን ስታነሳ ስልኳን አገኘችው። እንዳያገኝባት



ወጣት ህንደኬ ዳንኤል

በመደበቅ ወደ መታጠቢያ ቤት ለመግባት ስትነሳ ሰምቶ ምን እንደሆነች ጠየቀ። በዚህ ጊዜ ህንደኬ በህመም እጅግ በመረረ ሃዘን ውስጥ በመሆኗ መልስ እንኳን ለመስጠት አልፈለገችም፤ ከቻለ እንደውም ክፍሉን ለቆ እንዲወጣላት ጠየቀችው።

እሱ ግን ምንም እንዳልተፈጠረ የኔ ውድ እያለ ሊያቆላምጣት ሞከረ። ህንደኬ ግን በቀላሉ የምትመለስ አለመሆኗን ሲረዳም ክፍሉን ለቆ ወጣ። እሷም ለአክስቷ ልጅ በመደወል የሆነችውን ልትነግራት ስጀምር እሷ ግን በምላሹ እየቃዠች መስሏት ስልኩን ዘጋችባት።ደግማ በመደወል ቅዠት አለመሆኑን ከቻለች እንድትረዳት ጠየቀቻት፤ ይህንን ጊዜ የአክስቷ ልጅ በመደናገጥ የት እንዳለች ጠየቀቻት እሱንም ለመመለስ ቦታውን በትክክል ማወቅ ያስፈልግ ነበር። ነገር ግን ሁኔታው ከመከሰቱ በፊት ያየችውን የምትገምተውን ምልክት ነገረቻት።

የቀድሞዋ የትምህርት ቤት ጓደኛዋ ርብቃ ጋር እንደምታድር በሰው ተደውሎ የተነገራቸው እናቷም ስለደረሰባት ነገር ሰሙ፤ አሁን ያለችበትን ቦታ ማፈላለጉ ቀጠለ። ከብዙ ጥረት በኋላም ያለችበት ቦታ ተገኘ።

“ጋሻው ያለሁበትን አልቤርጎ ሊያሳይ እየመጣ እንደሆነ በመስኮት አየሁት ልክ ለእሱ በሩን እንደከፈትኩለት ጥቃቱ አዳክሞኝ ነበርና ራሴን ስቼ ወደኩ።ጋሻው በኋላ ላይ ፈፅሞ እንዳላገኘኝና ለታምራት አሳልፎ እንዳልሰጠኝ ሊክድና ታምራትን ሊያስመልጠው ቢሞክርም አልተሳካለትም ።ደፋሪዬ ታምራትም እጅ ከፍንጅ ለመያዝ በቃ። እኔም ለምርመራ ወደ ሆስፒታል ተላኩ። ሕክምና ምርመራ የመጣሁት የተደፈርኩበትንና የለበስኩትን ልብስ እንዳደረኩ ነበር። ሰውነቴን አልታጠብኩም። በመሆኑም የገዛ ሰውነቴ እጅግ ቀፈፈኝ። ሴትነት በጾታ ያጋመደን እህቶቼ ሆይ ራሴን በራሴ ተጠየፍኩት”።

የሕክምናው ጠበብቶች እንደሚሉት የሴቶች ድንግል ሦስት ዓይነት ነው። አንደኛው በተፈጥሮ ድንግልና የሌላቸው ሴቶች ያሉበት ነው።ሁለተኛ ከባድ ዕቃዎችን በማንሳት ምንም ሳይሆን በራሱ በተፈጥሮ የሚሄድ ድንግልናም አለ።ሦስተኛ በሕክምናው በተደፈረችበት ሰዓት ሳይሆን ከተደፈረች በኋላ በሦስተኛው ቀን የሚጠፋ (ብሊድ የሚያደርግ) ድንግልና ነው።በዚህ ምክንያት እያንዳንዱ የሕክምና ሂደት ለእኔ አድካሚና አሰልቺ ነበር በማለት ያለፈችበትን መንገድ ትናገራለች።

እያንዳንዱ ሂደት ከሕክምና ማስረጃ ጋር ተያይዞ ነው የሚከናወነው። ይሄን ለማወቅ በርካታ ጥያቄዎች ይደረጋሉ ። ፍቅረኛ አለሽ የለሽም? የሚሉና ብዙ ብዙ በዛን ሰዓትና ሁኔታ በፍፁም መጠየቅ አለበት ተብሎ የማይጠበቁ ጥያቄ ይነሳሉ። ለምሳሌ ፍቅረኛ አለሽ የለሽም? ተብሎ መጠየቅ አግባብ አለው ብዬ አላምንም የምትለው ህንደኬ ለዚህ ምክንያቷ ደግሞ አለኝ ከተባለ መርማሪዎቹ ከዛ በፊት የነበረ የጾታ ግንኙነት ታሪክ አለ ለማለት ይጠቀሙበታል።የወሲብ ልምምድ ስላላት በተከሳሹ ተደፍራለች ወይም ድንግልናዋን በመደፈር አጥታለች ብለው ስለማይገምቱ ስለመሆኑም ታብራራለች ።በተለይ የመደፈር ጥቃቱ የደረሰው ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በላይ የሆነች ሴት በህግ በኩል ምታገኘው ውጤት ብዙም አመርቂ አለመሆኑንም በቅሬታ ታነሳለች ።

“እኔ ስደፈር 18 ዓመቴ ነበር። በዚህ የተነሳ ይሁን በሌላ በማላውቀው ምክንያት ሰውዬው ከቤርጎው ሳይወጣ እጅ ከፍንጅ ቢያዝም የክስ ሂደቱ ከአራት ወራት በላይ ፈጅቷል። በእሱም ብሶ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ ድርጊቱን እሱ ሳይሆን ሌላ ሰው እንደፈፀመው ሁሉ ቆይ እስቲ እናያለን እያለ ይዝት ነበር። ዛቻ ብቻ ሳይሆን ዕድሜዬን ከፍ ለማድረግና ራሱን ከጥፋተኝነት ለማዳን ብዙ ሙከራዎችን አድርጓል። የተወለድኩበት ሆስፒታል፤እንዲሁም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን እማርበት የነበረ ትምህርት ቤት ድረስ በመሄድ ዕድሜዬን ከፍ አድርጎ ለማስወጣት ጥሯል።ፋይል ለማስጠፋትም በእጅጉ ተግቶ ነበር” በማለት የደረሰባትን ትናገራለች።

በሌላ በኩልም ትላለች ህንደኬ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ መጓተት እንዲፈጠር እሷም ተሰላችታ ሁኔታውን እንድትተወው በሚመስል መንገድ ሰውዬው አማርኛና ሌሎች ቋንቋዎች እየቻለ አማርኛ እንደማያውቅ በአስተርጓሚ ሀሳቡን የሚገልፅበት ሁኔታ እንደነበር ትናገራለች።

ይህ ሁሉ አሰልቺ ሂደት ቢታለፍም ህንደኬን የደፈረውም ሆነ ሁኔታውን ያመቻቸለት ጓደኛው ስምንት ዓመት ከአምስት ወር ተፈርዶባቸዋል።ግን በተፈረደባቸው አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለቱም ከእሥር ቤት ወጡ። ይህንን የተመለከተችው ህንደኬም ሆነች ቤተሰቦቿ ለምን ሲሉ ለመጠየቅ እንኳን ጊዜ ሳያገኙ አጥፊዎቹ ከሀገር ወጥተው ማምለጣቸውን ሰሙ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ከተፈጠረባት የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በላይ ጎዳት።ስቃይዋን አበረታው። ጥቃት ፍትህ ተፈፃሚ ያለመሆኑ በደል ፤በሀብታሞችና በድሆች ሰዎች መካከል ያለው ፍትህ የማግኘት ልዩነት ህንደኬን ከፍ ወዳለ የስነ ልቦና ችግር ውስጥ አስገባት።

“ዳግም ላይጠገን ልቤ ተሰበረ። በእጅጉ ደማ፤ ቆሰለ። በሰፈር፤ በትምህርት ቤት፤ በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር የነበረኝ ማህበራዊ መስተጋብር ውሃ የተቸለሰበት ያህል ሙሉ በሙሉ ቀዘቀዘ።ሳቂታና ተጫዋችነቴ ጠፋ። ራሴን የምረሳበት መንገድ እፈልግ ነበር።ለወንድ የነበረኝን ዕምነት አጣሁ።እንኳን አጠገቤ ላስጠጋቸው ከሩቅ ሳያቸው እሸሻለሁ። የ11ኛ ክፍል ትምህርቴን ደግሜ ለመማር ትምህርት ቤት ገብቼ ነበር።ሆኖም ከጓደኞቼ እኩል መሄድ አልቻልኩም። ልቤ በራሴ ችግር ጭልጥ ብሎ እየሄደ በድኔ ብቻ ቁዝም ብሎ መቀመጥ ሆነ።ማንም እንደማይረዳኝ አስብ ነበር። በነዚህና ራሴን እየሳትኩ በመውደቄ፤ ደጋግሜ በመታመሜ መዝለቅ አልቻልኩም።እናም በደረሰብኝ ተገዶ መደፈር መዘዝ ለሁለት ዓመታት ትምህርቴን አቋረጥኩ” ትላለች።

ህንደኬ ከጥቃቱ በፊት ዓላማ ፣ራዕይና ግብ ያላት ጎበዝ ተማሪ ነበረች። በዕድሜ በአንድ ዓመት ከሚበልጣት ወንድሟ ጋር ደረጃቸው አንድ እየሆነ ወላጆቻቸውና የሚማሩበት ትምህርት ቤት ለመሸለም ይቸገሩ ሁሉ ነበር ፤ ግን ጥቃቱ ከደረሰባት በኋላ ይሄ ሁሉ ጥንካሬና ብርታቷ ጠፍቶ ባዶ ቀረች። በጣም ስለተጎዳችም አንዳንድ ስም የሚጠየቅባቸው ቦታዎች ላይ ስትሄድ ራሱ ጭልጥ ብላ ስለምትጠፋ የገዛ ስሟ ይጠፋት ነበር።

የሕክምናው ሙያ እና ሕጉ ይሄን ሁሉ የተጠቂዋን የስነ ልቦና በደል የሚያገናዝብ አለመሆኑ አሁንም እንደሚንበለበል እሳት ያቃጥላታል።

ዛሬ ላይ በፈጣሪ እርዳታ በእናቷ ብርታት ወደ ራሷ ተመልሳለች ።”ነገሮች ከብደው ሲመጡ እንዴት ማቅለልና መቋቋም እንደሚቻል ከእናቴ ተምሬያለሁ። አርአያነቷ ወደ ራሴ እንድመለስ አድርጎኛል።መቼም ከጎኔ ተለይታኝ የማታውቀው ጓደኛዬም ለእኔ መለወጥ ድርሻዋ ብዙ ነው። ዛሬ ላይ 21 ዓመቴ ነው። 22ኛዬን ለመያዝም የጥቂት ወራት ናቸው የሚቀሩኝ።ትምህርቴን በጥቃቱ ካቋረጥኩ ከሁለት ዓመት በኋላ ቀጥዬ 12ኛ ክፍል አጠናቅቄያለሁ። ወደከፍተኛ ትምህርት ተቋምም ገብቼ ዘንድሮ የሶስተኛ ዓመት የነርሲንግ ተማሪ ነኝ” በማለት ከወደቀችበት መነሳቷን ትናገራለች።

አሁን ላይ ህንደኬ ሴቶችና ህፃናት ያልተገባና ሰዋዊ ባልሆነ ባህርይ ባላቸው ሰዎች እንዳይጠቁ የሚያግዝ መከርቻ ቻሪቲ ኦርጋናይዜሽን (MEKRECHA CHARITABLE ORGANIZATION) የተሰኘ ሴት ህፃናትን ብቻ ሳይሆን ወንዶችንም አስገድዶ ከመድፈርና ከተለያዩ ጥቃቶች የሚከላከል ድርጅት በመመስረትና ስራ አስኪያጅ በመሆን እየሰራች ትገኛለች።

“ህፃናት እንዲሁም ሴቶች ለጥቃት እንዳይጋለጡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየሰራሁ ያለሁት ከታናሽ እህቴ ጋር ነው። ለዚህ ዋናው ምክንያቴ ደግሞ እኔ ላይ የደረሰው ጉዳት ነው። በግሌ ጾታዊ ጥቃቱ ከደረሰብኝ በኋላ ወንድ ልጅ ከሴት ልጅ ገላ የዘለለ አመለካከት እንዳለው ያየሁበትም አጋጣሚ አለ።የደፈረኝ ወንድ የመሆኑን ያህል አሁን ላይ ድርጅቴ ራሱን ችሎ በሁለት እግሩ እንዲቆም በማድረጉ ረገድ በከፍተኛ ሁኔታ እያገዘኝ ያለውም የሥራ አጋሬ ወንድ ነው።ያልሆኑ ወንዶች እንዳሉ ሁሉ መልካም ወንዶችም አሉ”ትላለች። የእሷን ድርጅት ጨምሮ በርካቶች በሴቶች ጥቃት ላይ ብዙ ስራ እየሰሩ ቢሆንም ዛሬም በሴቶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት አልቆመም እንደውም ተባብሶ ቀጥሏል። ድብደባ፤መደፈር አንዳንድ ባሎችና የወንድ ጓደኞች የትዳር አጋራቸውን እስከመግደል የደረሰ ኢ ሰብዓዊ ድርጊት ሁሉ እየፈጸሙ ነው። ሆኖም በሕግ የሚጣለው ቅጣትም ሆነ በሌላ አካላት የሚወሰደው እርምጃ አስተማሪነቱ ላይ የብዙዎች ጥያቄ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ጥቃት የደረሰባቸውም ሆኑ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች እንዲሁም ሌሎች የችግሩን አሳሳቢነት የተረዱት አይመስልም ምክንያቱም አንድ ሰሞን ሆይ ሆይ ይባልና ሁሎም ነገር ይረሳል።ይህ ደግሞ ችግሩ ተዳፍኖ እንዲቀር ቀን እየጠበቀ እዚህም እዚያም እንዲፈነዳ እያደረገው ነው ትላለች ህንደኬ።

“እሳት በአንድ እንጨት ሳይሆን በብዙ እንጨት ጥምረቶች እንደሚነድ ሁሉ ጥቃቱን በጋራ ትግል ማስቆም ይገባል። ግለሰብ፤ቤተሰብ፤ የሕግ አካላት፤የሃይማኖት ተቋማት፤መምህራን ፤የነቃ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው።በግሌ እንዲህ ራሴን አሳልፌ እስከመስጠት በመድረስ ታሪኬን አርአያ አድርጌ እየታገልኩ እገኛለሁ።ሆኖም ትግሉ ቀላል አይደለም።በርካታ ባለሀብቶች፣ አንቱ የተባሉ ሰዎች ከጾታዊ ጥቃት ተነካክተዋል። በመሆኑም በሃሳብም ሆነ በገንዘብ መደገፍ አይፈልጉም። ማህበሩ በ2012 ዓ.ም ቢመሰርትም ድጋፍ አግኝቼ ቢሮ የከፈትኩት በቅርብ ነው” በማለት በዘርፉ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እየተገኙ ያሉ ድጋፎችም አመርቂ አለመሆናቸውን ትናገራለች።

# ማረፊያ

# አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በ1963 ዓ.ም የታተሙት የአዲስ ዘመን ጋዜጦች ለዛሬው ዓምዳችን የሰበሰብናቸው ቀደምት ዘገባዎች ትኩረት ናቸው።በዚያን ዘመን የነበሩ ኩነቶችን መለስ ብለን እንድናስታውስ ከሚያደርጉን የጋዜጣው ዘገባዎች መካከል ግርምትን የሚፈጥሩና ዛሬ ላይ ሆነን ስናያቸው ሊያዝናኑን የሚችሉም አሉ።አደጋዎች እና ወንጀል ተኮር ዜናዎችም ይገኛሉ፡፡በሮይተርስ የዜና ወኪል ተዘግቦ የነበረ ትንግርት የሚጭር አንድ ዘገባንም አካተን እንደሚከተለው መልሰን ለንባብ አቅርበናል።

### በባሌ ጠቅላይ ግዛት ጅብ ሁለት ልጆች በላ

ጐባ፤ (ኢ.ዜ.አ) በባሌ ጠቅላይ ግዛት በሐፍጀር ወረዳ ኗሪ የነበሩት የ፳ና የ፫ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ፪ ህፃናቶች በጅብ መበላታቸውን የኢልከሬ አውራጃ ግዛት ዋና ጸሐፊ አቶ ግዛው ጋሻው ገለጡ፡፡

መሐመድ ሁሴን ፤አብዲና ማህሙድ በደል የተባሉት እነዚህ ሕፃናቶች ባለፈው ነሐሴ ወር አጋማሽ ላይ በተለያዩ ቀናቶችና ሥፍራዎች በጅብ ተወስደው የተበሉት ሌሊት በወላጆቻቸው መኖሪያ ቤት ውስጥ ከተገኙበት ቦታ ላይ ነው፡፡

ጅቦቹ የቤቱን ግድግዳ ሰብረው ገብተው ሕፃናቶቹን ከመኝታቸው ላይ በወሰዱበት ወቅት፤ወላጆቻቸው የተቻላቸውን ያህል መከታተል አድርገው ሳይሳካላቸው በመቅረቱ ፤ሕፃናቶቹ መበላታቸው ታውቋል፡፡ከዚህም አስቀድሞ እነዚሁ ጅቦች ፤ቀንም ሆነ ማታ በአካባቢው የሚኖረው ሕዝብ ያረባቸውን የጋማና የቀንድ ከብቶች በመብላት በጣም ያስቸገሩበትን ያህል ፤ባሁኑ ወቅት ደግሞ ከእንስሳት ሰው ወደ መብላት በማዘንበላቸው፤ በአካባቢው ከፍ ያለ ሥጋት መፍጠራቸውን አቶ ግዛው ጋሻው በተጨማሪ ገልጠዋል።የሐፍጅር ወረዳ የሚገኘው በአልከሬ አውራጃ ግዛት ነው።

( መስከረም 9 ቀን 1963 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### የሰባት ዓመት ልጅ ተቃጥላ ሞተች

ነቀምቴ፤(ኢ-ዜ-አ) ፀሐይ ጀማነህ የተባለች የ፯ ዓመት ልጅ በአለፈው ነሐሴ ፳፮ ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ.ም በእሳት ተቃጥላ መሞቷን የቄለም አውራጃ ግዛት ጽ/ቤት ገለጠ፡፡

ይህ አደጋ የደረሰው በቄለም ወለጋ አውራጃ ተጆ ወረዳ ጐፊ በተባለው ቀበሌ ነው፡፡ልጅቱ በዚህ አደጋ ተቃጥላ የሞተችው ቤቱ ውስጥ እንዳለች ቤቱ በመቃጠሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

ይኸው የቃጠሎ አደጋ የደረሰባት የሣር ክዳን ቤት የአቶ ይማም አንቺላ ሲሆን፤ ቤቱን ያቃጠለው ወንድምዮው አቶ ማሻ አንቺላ መሆኑንም የአውራጃው ግዛት ጽ/ቤት በተጨማሪ አስታውቋል፡፡

(መስከረም 9 ቀን 1963 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### ፯ ጊዜ ቼክ አጭበረበረ የተባለው አሜሪካዊ ወህኒ ቤት ገባ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በመዘዋወር ሰባት ሰዎችን አጭበረበረ የተባለው አሜሪካዊ ተመስክሮበት ወህኒ ገባ።

ባርት ጆሐንሰን የተባለው የ፳፰ ዓመት ሰው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በባንኮ ዲሮማ የሌለውን ገንዘብ አለኝ በማለት ቼክ መስጠቱን የዐቃቤ ሕግ ክስ ያመለክታል፡፡

ተከሳሹ አጭበረበራቸው ተብሎ ከአቶ ክበበ ነፍሶ ፬፻ ብር፤ከአቶ ታኩ አበራ ፳፻፹ ብር፤ ከሸለቃ ዓለማየሁ ደስታ ፳፻ ብር፤ ከአክሱም የጉዞ ወኪል መ/ቤት ፩ ሺህ ፬፸፱ ፤እንዲሁም ከልዩ ልዩ ድርጅቶች መሆኑ ታውቋል፡፡

ኗሪነቱ በአዲስ አበባ ጐንደር ሆቴል የሆነው በርት ጆሐንሰን ወህኒ ቤት ከመግባቱ በፊት ለ፪ ሺህ ብር የሚበቃ ዋስ ቢያገኝ እንዲለቀቅ ተፈቀደለት፤ገንዘብ በማጣቱ ወህኒ ገብቷል፡፡አሜሪካዊው ጐረምሳ ኅዳር ፰ ቀን አዲስ አበባ ፍ/ቤት ፬ኛ ወንጀል ቀርቦ ምስክር መሰማት ጀምሯል፡፡ተከሳሹ የፍርዱ ሁኔታ እስኪታወቅ ወህኒ ቤት ተመልሷል።

(ኅዳር 10 ቀን 1963 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

### የነብር ቆዳና የዝሆን ጥርስ ይዘው የተገኙ ተቀጡ

መቱ፤(ኢ/ዜ/አ) ስለ ዱር አራዊት ጥበቃ የወጣውን ደንብ በመተላለፍ ፪ሺህ ፳፻ ብር ግምት ያላቸው የነብር ቆዳና የዝሆን ጥርስ ይዘው የተገኙት አቶ አውጋቸው ተከተል ፴ ተቀጥተው በእጃቸው የተገኘው ንብረት በውርስ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ተወሰነ፡፡አቶ አውጋቸው፤፬ የነብር ፪ የጨኖ ቆዳዎችና ፪ የዝሆን ጥርስ ይዘው የተገኙት በቡኖ አውራጃ በበደሌ ከተማ ነው፡፡

ተከሳሹ በፈጸሙት የደንብ መተላለፍ ጥፋት አድራጐታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠ ፤፴ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ፤ገንዘቡን መክፈል ባይችሉ በ፪ ወር እሥራት እንዲቀጡ የቡኖ ወረዳ ፍርድ ቤት ቃል አቀባይ አስታውቋል፡፡

(ኅዳር 20 ቀን 1963 ከታመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

ከታረደች ፍየል ሆድ ዕቃ ውስጥ ማዕድን ተገኘ

ሌጐስ፤ (ሮይተር) በናይጄሪያ ውስጥ አንድ ፍየል

### ከታረደች በኋላ ፤በጨጓራው ውስጥ ልዩ ልዩ የማዕድን ሀብት እንደተገኘ የደረሰን ዜና ገለጠ

በፍየሏ ጨጓራ ውስጥ የተገኘው ፤የወርቅ እንክብሎች፤ልዩ ልዩ ውድ የሆኑ የጌጣ ጌጥ መሣሪያዎች ፤ገንዘብ፤ ዶቃና ጨሌ የመሳሰሉት የአገሬው ጎሣ ጌጣ ጌጥ ናቸው፡፡

እነዚህ ጌጣ ጌጦች ሊገኙ የቻሉት በአገሩ የባህል ደንብ መሠረት አንድ ሰው ሲሞት በእሱ ቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ፍየል ይታረዳል።ይህም እንደ መሥዋዕት የሚቆጠር ሲሆን፤ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ሲገኝ ደግሞ የመጀመሪያው ነው ተብሏል፡፡ከፍየሏ ጨጓራ የተገኘው ሀብት የማን ንብረት እንደሚሆን የደረሰን ዜና አላረጋገጠም።

( ጥቅምት 22 ቀን 1963 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ የአውሮፓ ህብረት ያወጣውን የነዳጅ ዋጋ ተመን እንደማትቀበል አስታወቀች

ሩሲያ የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ያወጡትን የነዳጅ ዋጋ ተመን እንደማትቀበል አስታውቃለች። የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ሩሲያ የነዳጅ ምርቷን በበርሜል 60 የአሜሪካ ዶላር እንድትሸጥ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ይፋ አድርገዋል።

በስምምነቱ መሰረትም የህብረቱ አባል ሀገራት ከሩሲያ ነዳጅ በበርሜል ከ60 የአሜሪካ ዶላር በላይ እንዳይገዙ እገዳ ተጥሏል።በተመሳሳይ የቡድን ሰባት አባል ሀገራት እና አውስትራሊያ ከሩሲያ ነዳጅ ከተጠቀሰው ዋጋ በላይ እንደማይገዙ አስታውቀዋል።

የሩሲያ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አሌክሳንደር ኖቫክ ጉዳዩን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ፤ ሩሲያ የአውሮፓ ህብረትም ሆነ የቡድን ሰባት አባል ሀገራት በነዳጅ መሸጫ ዋጋ ላይ ያወጡትን ተመን አትቀበልም ብለዋል።

የአውሮፓ ህብረት ያወጣው የዋጋ ማሻሻያ በሞስኮ ላይ ችግር እንዳያስከትል የተለያዩ አዋጭ መፍትሔዎች ላይ እየተሰራ እንደሆነ መግለጻቸውንም አር ቲ ዘግቧል። በአንጻሩ ሩሲያ የነዳጅ ገበያውን በተመለከተ ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ለመግዛት ከሚስማሙ ሀገራት ጋር በቅንጅት እንደምትሰራ ነው የተናገሩት።

ሀገራት በሩሲያ ነዳጅ ዋጋ ላይ ያወጡት የዋጋ ተመን ዓለም አቀፍ ገበያውን እንደሚያውከው የገለጹት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሀገራቱ አካሄድ ዓለም አቀፉን የንግድ ሕግ እንደሚጻረርም መናገራቸውን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

የሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ከተጀመረ ስድስት ወራት ቢያልፈውም ጦርነቱ በዓለም ምግብ እና ነዳጅ ዋጋ ላይ ጭማሪ እንዲመዘገብ ምክንያት ሆኗል። ጦርነቱ በዓለም ዲፕሎማሲ ላይ የተለያዩ መፋለሶችን ያስከተለ ሲሆን ሀገራት ከትብብር ይልቅ ጎራ ለይተው እንዲሰለፉ እያደረገም ይገኛል።

አሜሪካ እና የአውሮፓ ህብረት በሩሲያ ዩክሬን ጦርነት ላይ በተለያየ መንገድ በመሳተፍ ላይ ሲሆኑ በሩሲያ ላይ ከስድስት ሺህ በላይ ማዕቀቦችን ጥለዋል። ሩሲያም የአጸፋ እርምጃ በመውሰድ ላይ ስትሆን ማዕቀቡ ለአውሮፓ ሀገራት የምታቀርበውን ጋዝ ሽያጭ እክል አስከትሏል።



ይሄንን ተከትሎም 40 በመቶ ለሚሆኑ የአውሮፓ ሀገራት ነዳጅ ስታቀርብ የነበረችው ሩሲያ በማዕቀቡ ምክንያት ለአውሮፓውያን ነዳጅ መላክ አለመቻሏን በተደጋጋሚ ገልጻለች። በዚህ ሳቢያም በነዳጅ ዕጥረት እየተፈተነ ያለው የአውሮፓ ህብረትም በሩሲያ ላይ የጣለውን ማእቀብ እስከማላላት ቢደርስም በሩሲያ ላይ የተጣሉት ሁሉም ማዕቀቦች እስካልተነሱ ድረስ ሩሲያ ምንም አይነት ነዳጅ እንደማትልክ ራሺያ ቱዴይ ዘግቧል።

## ኢራን ለእስራኤል ሰልለዋል ያለቻቸውን አራት ዜጎች በስቅላት ቀጣች

**በጋዜጣ ሪፖርተር**

ኢራን ከእስራኤል የስለላ ድርጅት ጋር ተመሳጥራችኋል ያለቻቸውን አራት ዜጎች በስቅላት ቀጣች።የኢራን መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት የኢራን ዜግነት ያላቸው አራቱ ወንዶች በሞት የተቀጡት ከትናንት በስቲያ እሑድ ነው። የኢራን ፍርድ ቤት በአራት ሰዎች ላይ የሞት ቅጣቱን ያጸናው ባለፈው ረቡዕ ነበር። አራቱ ዜጎች በቁጥጥር ሥር የዋሉት ደግሞ ባለፈው ግንቦት ወር ነው።

ይህ የሞት ቅጣት ተፈጻሚ የሆነበት ወቅት በኢራን ላለፉት አራት ወራት የተደረገውን ጸረ መንግሥት ተቃውሞ ተከትሎ ነው። ከአራቱ ዜጎች ስቅላት ሌላ ሌሎች ሦስት ዜጎች ከአምስት እስከ አሥር ዓመት እስራት ተፈርዶባቸዋል። ሦስቱ ዜጎች የተከሰሱት ዜጎችን በማፈን ተግባር ተባባሪ በመሆናቸው፣ ፍቃድ የሌለው የጦር መሣሪያ በመያዝ እና ሌሎች የደኅንነት ደንቦችን በመጣሳቸው እንደሆነ የአገሬው ራዲዮ ዘግቧል።



እስራኤል ከሌሎች አካባቢው ካሉ አረብ አገራት ጋር ግንኙነቷን አሻሽላለች። ይሁንና ከኢራን ጋር አሁንም ደመኛ ጠላቶች ናቸው። በገሀድ ጦርነት ባያካሄዱም በስለላው ዓለም አንዳቸው ለሌላቸው ተኙተው አያውቁም።ሰዎችን በማፈን በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው የእስር ብይን ከተላለፈባቸው መሀል አንዱ የእስራኤል ሚዲያ ከወር በፊት የኢስላሚክ አብዮታዊ ዘብ አባል ነኝ የሚል ሰውን አቅርበው የእስራኤል ዲፕሎማቶችን በአውሮፓ የመግደል ሴራ እንደነበረ ከተናዘዘበት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው።

ኢራን ይህ ሰው ተራ ገበሬ ነው፤ አንድ ‘ወሮበላ ቡድን’ እንደ አውሮፓዊያኑ በ2021 ካገተው በኋላ ያንን እንዲል አስገድደውት ነው ትላለች። ኢራን አሁን በአገሯ የተቀሰቀሰውን ከፍተኛ አመጽ በማቀጣጠል አሜሪካና እስራኤልን ትከሳለች። አመጹ የተቀሰቀሰው የሞራል ፖሊስ በሴቶች ላይ እየፈጸመ ያለውን ተግባር በመቃወም ነው።

በቅርብ ጊዜ በኢራን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ዘለግ ላለ ጊዜ የሰነበተው ይህ አመጽ በመላ አገሪቱ ተስፋፍቶ ቆይቷል።የኢራን ፍርድ ቤት ከአመጹ ጋር በተያያዘ 6 ሰዎች ላይ የሞት ቅጣት ውሳኔ አሰጥቷል። አምነስቲ በበኩሉ 21 የሚሆኑ ሰዎች በስቅላት ሊቀጡ ይችላሉ ሲል ስጋቱን ገልጧል። የመብት ተሟጋቾች እንደሚሉት ኢራን በዓለም ከቻይና በስተቀር የትኛውም አገር በስቅላት ቅጣት ተፈጻሚ በማድረግ የሚስተካከላት የለም ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ማክሰኞ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኢትዮጵያውያን ሴት አትሌቶች ወርቃማ የማራቶን ዘመን

**ቦጋለ አበበ**

በመም ውድድሮች ጠንካራና ውጤታማ የሆኑ በርካታ ሴት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፊታቸውን ወደ ማራቶን ውድድሮች አዙረው የአርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ፉክክሩ ላይ ጎልተው እየወጡ ይገኛሉ። በመም ውድድሮች ብዙ ስኬት የሌላቸውና መነሻቸውም ማራቶን የሆነ በርካታ ሴት አትሌቶችም በታላላቅ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ብዙ ድሎችን ሲያስመዘግቡ ታይተዋል።

ከሌሎች ውድድሮች በተለየ ለግምት እንኳን አስቸጋሪ በሆነው የማራቶን ውድድር ኢትዮጵያውያን ሴት አትሌቶች በተለያዩ አለም አቀፍ ውድድሮች በስኬት የተንበሸበሹበት አመት ቢኖር የዘንድሮው በጉልህ መጠቀሱ የግድ ነው። እንስቶቹ ኢትዮጵያውያን በርቀቱ በርካታ አለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ከማሸነፍ በዘለለ ፈጣን ሰአቶችን ማስመዝገብ መቻላቸው ወርቃማ የማራቶን ዘመናቸው ላይ እንደሚገኙ ማሳያ ነው።

ባለፈው ክረምት በፖርትላንድ ኦሪገን ከተካሄደው የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ሴት አትሌቶች በርካታ የማራቶን ድሎችን አስመዝግበዋል። የ27 አመቷ ድንቅ አትሌት በአለም ቻምፒዮናው ስታሸንፍ የቻምፒዮናውን ክብረወሰን በ2:18:11 በማሻሻል ጭምር ነበር። ከዚህ ታላቅ ስኬት በተጨማሪ ባለፉት ስምንት ወራት ብቻ የኢትዮጵያ ሴቶች የማራቶን ክብረወሰን ሶስት ጊዜ በተለያዩ አትሌቶች ተሻሽሏል።

ባለፈው ሚያዝያ በሃምቡርግ ማራቶን አትሌት ያለምዘርፍ የኋላው ከ2019 ወዲህ የኢትዮጵያን የማራቶን ክብረወሰን በ2:17:23 አሻሽላለች። ይህም በርቀቱ የአለም ሁለተኛው ፈጣን ሰአት ሆኖ ተመዝግቧል። ባለፈው መስከረም መጨረሻም ይህ የኢትዮጵያ የርቀቱ ክብረወሰን በአትሌት ትእግስት አሰፋ በርሊን ማራቶን ላይ ከሁለት ደቂቃ በበለጠ ሊሻሻል ችሏል። 2:15:37 የሆነው ሰአት የኢትዮጵያ አዲስ ክብረወሰን ከመሆኑ በዘለለ የአለም ሁለተኛው ፈጣን ሰአትም ነበር።



አትሌት አማኔ በሪሶ የኢትዮጵያን የማራቶን ክብረወሰን 2:14:58 በሆነ ሰአት አሻሽላለች

በበርሊን የተመዘገበው ይህ የኢትዮጵያ የማራቶን ክብረወሰን ከሁለት ወር በኋላም ከትናንት በስቲያ ቫሌንሲያ ማራቶን ላይ እንደገና ተሻሽሏል። የክብረወሰኑ ባለቤት የሆነችው የ31 አመቷ አትሌት አማኔ በሪሶ 2:14:58 በሆነ ሰአት ስታሸንፍ ሁለተኛው የርቀቱ የአለም ፈጣን ሰአት ሆኗል። ይህ ሰአት አትሌቷ የራሷንና የቫሌንሲያ ማራቶን ክብረወሰንን ከአምስት ደቂቃ በበለጠ ያሻሻለችበት ሲሆን በኬንያዊቷ የኦሊምፒክ ቻምፒዮን ፕሬስ ጂፕቺርቺር ከተያዘው የአለም ክብረወሰንም በ54 ሰከንዶች ብቻ የዘገየ ነው።

በዚሁ ውድድር ትልቅ ትኩረት አግኝታ የነበረችው የአለም የ10ሺ ሜትር ቻምፒዮኗ አትሌት ለተሰንበት ግደይ በማራቶን የመጀመሪያዋን ፉክክር አድርጋ ሁለተኛ ነው ያጠናቀቀችው። ያስመዘገበችው 2:16:49 ሰአት ግን በመጀመሪያ የማራቶን ውድድር ከተመዘገቡ ሰአቶች ፈጣኑ በመሆን አትሌቷ ወደ ፊት በርቀቱ ትልቅ ታሪክ መስራት እንደምትችል ፍንጭ የሰጠ ነው።

ለተሰንበት በመጀመሪያ የማራቶን ውድድር ተሳትፎ በታሪክ ፈጣኑን ሰአት ቫሌንሲያ ላይ ከማስመዝገቧ ከሶስት ሳምንታት በፊትም ኢትዮጵያዊቷ የኦሊምፒክና የአለም ቻምፒዮና የ10 ሺ ሜትር ባለ ድል አልማዝ አያና ተመሳሳይ ታሪክ መስራት እንደቻለች ይታወሳል። አልማዝ ከሶስት ሳምንት በፊት በአምስተርዳም ማራቶን በርቀቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ተወዳድራ 2:17:20 በሆነ ሰአት ስታሸንፍ ያስመዘገበችው ሰአት በርቀቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በተፎካከረች አትሌት የተመዘገበ ፈጣኑ ሰአት ነበር። በመም ውድድሮች ብርቱ ተፎካካሪዋ የሆነችው አትሌት ገንዘቤ ዲባባም በርቀቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ተወዳድራ አልማዝን ተከትላ ሁለተኛ ስታጠናቅቅ ያስመዘገበችው 2:18:05 ሰአት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እንደ አጠቃላይ ከአለማችን ሃያ ፈጣን የሴቶች ማራቶን ሰአቶች አስሩ የተመዘገቡት በኢትዮጵያውያን አትሌቶች ነው። ከነዚህ አስር ፈጣን ሰአቶች ውስጥ ስድስቱ የተመዘገቡት ደግሞ በ2022 የውድድር አመት ነው። ቀዳሚ ሆነው የተቀመጡት ሁለት ፈጣን ሰአቶች በኬንያውያን አትሌቶች የተመዘገቡ ቢሆንም አንዱና ዋነኛው የአለም ክብረወሰን ከሶስት አመት በፊት ነው የተመዘገበው። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በዚህ የውድድር አመት የማራቶን ወርቃማ ጊዜ እያሳለፉ ይገኛሉ ቢባል አልተጋነነም። ይህም በቅርብ ርቀት እየተከተሉት የሚገኘውን የአለም የማራቶን ክብረወሰን ለመስበር ብዙ ጊዜ ላይፈጅባቸው እንደሚችል ተስፋ የሰጠ ሆኗል።

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

# የግብርና መካናይዜሽንን ለማስፋፋት የኅብረት ስራ ማህበራት ሚና

**በዳኛቸው ቀደማቸው**

የኅብረት ሥራ ማህበራት የአርሶ አደሩንና የአርብቶ አደሩን ምርታማነት ለማሻሻል በግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በሀገሪቱ ለተመዘገበው የምርትና ምርታማነት እድገት የማህበራቱ ሚና ተጠቃሽ እንደሆነም ይታወቃል። ማህበራቱ ግብርናውን ወደ መካናይዜሽን ለማሳደግም እየሠሩ ይገኛሉ። ይሁንና የተሰሩት ሥራዎች ግን በቂ እንዳልሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአርሶና አርብቶ አደሩ አካባቢ ያሉ የህብረት ሥራ ማህበራትን በመጠቀም የትኩረት አቅጣጫውን ግብርናውን ማዘመን ላይ አድርጓል። በዚህም ባለፉት አምስት ዓመታት ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት የድህረ ምርት ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ የተከናወኑ ተግባሮች በቂ ባይባሉም ተስፋ የሚጣልባቸው እንደሆነ ይገለጻል። ግብርንና በማዘመን የግብርና መካናይዜሽንን በማስፋፋት ረገድ የተሠራው ሥራ እዚህ ግባ የሚባል አለመሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይም ድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ዘመናዊ መንገዶችን በመጠቀም ረገድ ሲከናወኑ የነበሩት እንቅስቃሴዎች የተቀዛቀዙ መሆናቸውን ተከትሎ አርሶ አደሩ ብዙ ደክሞ ያገኘው ምርት ለከፍተኛ ብክነት እየተዳረገ መሆኑን ነው የኮሚሽኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን እና በክልልና በከተማ አስተዳደሮች የኅብረት ስራ ኤጀንሲዎች ጥረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶ በርካታ ስራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። አርሶ አደሩ በምርት ወቅትና በድህረ ምርት ውጤታማነቱን ሊያሳድጉ የሚችሉ በሀገር ውስጥ የተመረቱም ሆነ ከውጭ የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን



ማስፋፋትና በማህበራቱ በኩል ማዳረስ እንዲቻል የተጀመሩት እንቅስቃሴዎች አጥጋቢም ባይሆኑም ተስፋ ሰጪ ውጤቶች የታየባቸው ናቸው።

ኅብረት ስራ ማህበራቱ እስካሁን በግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት የቅድመ እና የድህረ ምርት አገልግሎት መስጫ ማሽነሪዎችን በመያዝ አገልግሎቱን እየሰጡ ይገኛሉ። በዚህም እነዚህን መሳሪያዎች ለማግኘት አርሶ አደሩ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ ለምርት ወቅትና ድህረ ምርት አገልግሎት የሚያደርገውን ወጪ 25 በመቶ ለመቀጠብ ተችሏል።

ባለፉት አምስት ዓመታትም በተለይ ለድህረ ምርት መሰብሰቢያ የሚጠቅሙ ኮምባይነሮችንና መውቂያዎችን ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ እየሰሩ ያሉ የህብረት ስራ ዩኑየኖች አበረታች ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች ይጠቅሳሉ። ለአብነት ያህል ሎሜ አዳማ፣ገደብ አሳሳ፣ ኢጦሳ፣ ኡታ ዋዩ፣ አምቦ፣ ራያ ዋከና፣ሞጣ ፣የውላ፣ ፅሃይ፣መርከብ፣ መገናኛ፣ ወደራ፣ ከሰም፣መሊቅ፣ ዋልታ፣ ሃላባ እና መንቸኖ ሁለገብ ኅብረት ስራ ዩኒዬኖች የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዙ አስረድተዋል። ከዚህ አንፃር አርሶ አደሮች ብዙም ርቀው ሳይሄዱ በኅብረት ስራ ማህበሮቻቸው አማካኝነት በኩል የማረስ፣መሰብሰብና ማጨድ አገልግሎት እያገኙ ነው።

በኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን በኩል ሰፊ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ በመግለጽ፣ በግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁስን ለመግዛት ለሚፈልጉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከልማት ባንክ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

መንግስት ግብርናን ከማዘመን አኳያ በትኩረት መያዝ ያለበት ኅብረት ስራ ማህበራትን የግብርና መካናይዜሽን ተጠቃሚ የማድረግ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ የስትራቴጂክ ሰብሎች ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር እየተሰራ ያለውን የገበያ መር የግብርና ልማት አርሶ አደሩ በፍጥነት እየተቀበለው በመሆኑ ምርትን በጥራትና በብዛት ለገበያ ለማምረት በዋናነት አካባባቢን መሠረት ያደረገ የግብርና መካናይዜሽን እንዲስፋፉ እድል ይሰጣል። ይህንን የአካባቢ ስፔሻላይዜሽን መሠረት ያደረገ የኅብረት ስራ ማህበራት ግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥን በማሳደግ ግብርናን የማዘመን እንቅስቃሴ ቢደረግ ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ይመጣል። በተለይም አነስተኛ ጉልበት የሚጠቀሙ መሳሪያዎች አቅርቦትን በከፍተኛ ሁኔታ የማሳደግ፣ በስፋት የማስተዋወቅና ወደ ተግባር እንዲገባ በልዩ ትኩረት መስራት ይገባል። የቅድመ ምርትና ድህረ-ምርት የግብርና መካናይዜሽን አገልግሎት ለአርሶ አደሩ የሚሰጡ አካላትን የማደራጀትና በዚህ ስራ የተሰማሩ ህብረት ስራ ማህበራት በስልጠና የማገዝ፣ የብድር ስርዓት እንዲመቻችላቸው በማድረግ በመስኩ ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥ ርብርብ መደረግ አለበት።

በተሰጠ ልዩ ትኩረት እና የባለድርሻ አካላት ቅንጅት አርሶ አደሮች የግብርና ሥራቸውን ለማዘመን ከፍተኛ እገዛ የሚያደርጋቸውን የትራክተር ባለቤት እየሆኑ ነው። አርሶ አደሮቹ ለዘመናት በባሕላዊ መንገድ ብቻ ሲሠሩ በመቆየታቸው ከቆይታቸው አንጻር ሕይወታቸውን ሊያሻሽሉ እንዳልቻሉ ሲናገሩ ይሰማል። በልማት ለውጥ ብልፅግና ለማምጣት ቴክኖሎጂን መጠቀም ወሳኝ ነው። ማህበራቱ የግብርና መካናይዜሽንን በመጠቀም የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ መንቀሳቀስ መጀመራቸው የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነት ከማረጋገጥ አንጻር ጥሩ ጅምር ተደርጎ ይወሰዳል። የግብርና መካናይዜሽን ጉዳይ መንግሥትም በትኩረት ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። መንግሥት መካናይዜሽን ላይ እንደሚሠራ የሚገልጸውን ያህል በፋይናንስ አቅርቦት፣ በሥልጠና እና ሌሎች ድጋፎች ላይም መሥራት ይኖርበታል። ሥራውን በራሱ እስከሚሠራው ድረስም የማህበራቱን ጥረት ላቅ ያለ ደረጃ ላይ ለማድረስ ተጨባጭ ድጋፍ በማቅረብ መሥራት ይኖርበታል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et